-9-

ሰቆቃ

ከረን ሰንደርስ ዝናቡ አይሎ ዶፍ መውረድ ጀምሮ ነበር። በቀጥታ የሄድነው ወደ ሁለተኛው ሠራዊት ቀዳሚ መምሪያ ነበር። ከበረንዳ ላይ የቀረበልንን አምቦ ውሃ እየተጎነጨን ሁላችንም የሚወርደውን ዝናብ አንደ ቲያትር ፊዘን አንመለከታለን። ከቅጠሎች ላይ ኮለል ብለው የሚወርዱት የውኃ ጠብታዎች እና ከጣሪያው መጨረሻ ቀጥተኛ መስመር ሰርቶ የሚወርደው የዝናብ ውኃ ሃሳቤን እያነሆለሉ የቀኑን ትንግርት ያሳዩኝ ጀመር። አጋሮ መንገድ ላይ እጁን ዘርግቶ የወደቀው ወንበዴ፣ አይኖቻቸውን ወደ ሰማይ ተክለው ሣሩ ውስጥ የወደቁት፣ ወደ ገቦቹ፣ በመኪና ተጭነው ይሄዱ የነበሩት ቁስለኞች፣ ከወደ ጎን ተገንጥለው ሲሄዱ የእጅ ቦንብ የተወረወረባቸው ሁለቱ ወታደሮች ሁሉ በተከታታይ በዓንጎሌ ተመላለሱ።

"አሁን ዝናቡ እያየለ ከመጣ ከፍተኛ የመልሶ ማጥቃት ሙከራ እንደሚያደርጉ ጥርጥር የለውም።" ሲል ጀ/ደምሴ ከኃላቤ ባንኜ ነቃሁ።
"አዎን ተሸሎክልኮ ተጠግቶ የእጅ ቦንብ ለመወርወርም አመቺ ነው" አለ አንደኛው መኮንን። ወንዙ ዳር ድልድይ የጫነ ከባድ መኪና

አስኪያሻግራቸው ድረስ ይጠብቁ የነበሩት ዋዞች አዚያው በረንዳ ላይ አንደተቀመጥን ተከታትለው ገቡ። ዝናቡ አንደማባራት ብሎ ነበር። ጀ/ደምሴ ከመቀመጫቸው ተነሳና
"እኔ ወደ ሆስፒታል ሄጀ ቁስለኞችን አገበኛለሁ። አናንተ አዚሁ ቆዩ፤ ማታ አንገናኛለን" ብሎ የቀሩትን ተሰናበተና ወደመጡት መኪኖች አመራ። እኔ ሻ/ጌታሁንን ተከትዬ ከኋላ ገባሁ።

ከረን ሆስፒታል ሰንደርስ ከመግባታችን በፊት ሐኪሙ ተጠራና መጣ።
"እንደምንአለህ? አንተን ነው ከዚህ በፊት ያገኘሁት?" አለ ጀ/ደምሴ - ፊቱ አለመጠን ተኮሳትሮ የሚናገረውን ሁሉ የቁጣ ዓይነት ያስመስለዋል።
"አዎን ጌታዬ፣ እኔን ነው ያገኙኝ" ብሎ ሐኪሙ ሰላምታውን መለሰ ።
"እንዴት ነው ጠቅላላ ሁኔታው? ለመሆኑ በቂ ሰው አለህ?" አለ ድምፁን ረጋና ዝቅ አድርጎ።
"አዎ ጌታዬ በቂ የሰው ኃይል አለን። ከአቅማችን በላይ የሆኑትን ወደ አስመራ ልከናል፣ እነሱም ከባድ አደጋ የደረሰባቸው ናቸው"
"እስከ አሁን ምን ያህል ናቸው አስጊ ደረጃ ላይ ያሉት?" አለ ጀ/ደምሴ ከበፊቱ የበለጠ ፊቱን አጥቁሮና አኮሳትሮ።
"ወደ ዘጠና የሚሆኑት አስጊ ሁኔታ ላይ ናቸው። እነሱም በሙሉ ወደ አስመራ ተልከዋል፤ አዚህ የቀሩት ሶስት መቶ ሃምሳ አራት ቁስለኞች ናቸው።"
"አስጊ ያልሆነ ነው ብላችሁ ካቅማችሁ በላይ የሆነውን አዚህ አታስቀምጡ። አዚህ ለመርዳት የምትችሉ መሆናችሁን ትንሽ እንኳ የምትጠራጠሩት ካለ ወደ አስመራ መላክ አለባችሁ። ከዚህ በፊት ቀላል አደጋ የደረሰባቸው

ናቸው ተብለው የተተው ሁለት ሰዎች መሞታቸውን ሰምቻለሁ። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በምንም ዓይነት ሊደገም አይገባውም። አሁን የሚያስፈልገውን ሁሉ እደረጋችሁላቸዋል?"

"አዎን ጌታዬ አስፈላጊውን ሁሉ አድርገናል"

"እሺ ጥሩ ነው በየት ነው መግቢያው?" ብሎ ሲጠይቅ ሐኪሙ ከፊት ፊት እየመራ ወደ አዳራሹ መግቢያ አደረሰን። ጀ/ደምሴ ከበሩ ትንሽ ቆም አለና፣ በዝግታ አርምጃ ወደ ውስጥ ገባ። እኛም ተከተልን።

አዳራሽ ውስጥ ሁለት አርምጃ እንደ ተራመድኩ ሳላስበው አፍንጫዬን በእጄ ግጥም አርጌ ስይዝ የአባቴ ዓይን ድንገት ገረመመኝና ቀሰ ብዬ እጄን ወደ ቦታው መለስኩ። ቤቱ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ፣ በየትኛውም የመግባቢያ መንገድ ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው። በተለይ በአካል ቦታው ተገኝቶ የተመለከተ ሰው ምንጊዜም የማይጠፋ ሥዕል በጭንቅላቱ ቀርጾ ይኖራል።

ቁስለኞቹን በሶስት ረድፍ በተዘረጉ አልጋዎች ላይ አስተኝተዋቸዋል። የአብዛኞቹ ልብስ ወልቆ ግማሽ ሰውነታቸው ወይ ቁስል የሌለበት አካላቸው ብቻ ብርድ ልብስ ለብሶ የቀረው ባደውን ነው። ቤቱ አለቅጥ ታፍኗል። እንኳን በሽተኛ ጤነኛም የሚታመምበት ክፍል ነው። ሆዳቸውን የተመቱት ለመሸናት እንዲችሉ ፕላስቲክ ቱቦ በየብልታቸው ገብቶላቸዋል። በአጠቃላይ የዚህ ዓይነት አሰቃቂና አሳዛኝ ነገር በሕይወቴ አይቼ አላውቅም።

ጀ/ደምሴ በዝግታ እያንዳንዳቸውን ጠጋ እያለ እየተመለከተ ሲያልፍ አንደኛው ቁስለኛ

"ችግር አለ! ችግር አለ!" አለ ስቃይ በዋጠው ድምፅ።

"ምንድነው ችግርህ? ዶክተር ና አስቲ ወዲህ አርዳታ ይፈልጋል መሰለኝ" አለ ጀ/ደምሴ ቁስለኛው የሚለው ለማዳመጥ ጆሮውን ወደ ሰውየው አስጠግቶ።

"ፖፖ" አለ ቁስለኛው። አሁንም በዝግታ።

"በሉ በየደቂቃው እየተዘዋወሩ ችግራቸውን የሚጠይቋቸው ሰዎች እንዲመደቡ። ቶሎ አርዱት አባካችሁ" አለና "የምትጠይቁትን ሁሉ በተቻለ ለሚሟላት እንሞክራለን። አይዟችሁ!" ብሎ ወደ ሚቀጥለው ቁስለኛ አለፈ። ፊቱ ጠቅላላ በእሳት የተቃጠለ ይመስላል። የእጅ ቦንብ መቶት ሊሆን እንደሚችል በኋላ ተረዳሁ። የሚተነፍሰው ሁለት ቀዳዳ ያላቸው ፕላስቲክ ነገሮች ጉሮሮው ውስጥ ገብቶለት ነው።

"ይሄ ቁስለኛ አስመራ ቢሄድ አይሻልም?" አለ ጀ/ደምሴ የሰውየው ጉዳት አስካሁን ካየው ሁሉ አሰቃቂ ስለሆነበት።

"አዎ ነገ ልንልከው አስበናል።" አለ ሐኪሙ። ጀ/ደምሴ ክታች ወደ ላይ እንደ "ቅድም ምንድነው ያልከው" በማለት ዓይነት ገረመመውና ጭንቅላቱን ነቅንቆ ወደሚቀጥለው አለፈ።

ቁስለኞችን አንድ ባንድ እያየን መሀል አካባቢ ሰንደርስ አንድ የሚያቃስት ድምፅ ሰማና ጀ/ደምሴ ወደ ሰውዬው ጠጋ አለ።

ሰውዬው የተወሰኑ ቃላትን ሊያወጣ እየሞከረ በሰቃይ ምክንያት ሊናገር ያልቻለ ይመስላል።

"ምን ቆመህ ታየዋለህ አጁን የሚያስደግፍበት ነገር አምጣለት! የዚህን ዓይነት ቁስል እያየህ እንዴት ዝም ብለህ ታየዋለህ?" አለ። ድምፁን ዝቅ አድርጎ። ቁስለኛው ሁለቱም ብብቱ ሥር በጥይት ተመቶ ፋሻ የታሰረለት

ሲሆን እጆቹን ወደጎን ካልዘረጋ በቀር ቁስሉን እየነኩ ስለሚያስቸግሩት እጆቹን ሲዘረጋ የሚደግፈው ነገር ፈልጎ ነበር። ብዙ ጊዜ ዘርግቶ የደከመውና ቁስሉ እየተነካበት የሚሰቃይ መሆኑን ስናይ የሁላችንም ልብ ተነካ። ከአንጨት የተሰራ ድጋፍ እስኪ መጣለት እጁን ወደ ጎን ዘርግተው ሁለት ወታደሮች ያዙለትና ማቃሰቱን አቆመ።

በአዳራሽ ውስጥ እንዲሁ አንድ ባንድ ቁስለኞቹን እያየን ስናልፍ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በድኔ እንጂ እኔ የምንቀሳቀስ መስሎ አልሰማ አለኝ።

ከአዳራሹ እንደወጣን ጀ/ደምሴ ወደ ሐኪሙ ዞር አለና "በል በነገው አለት የባሰባቸውን ወደ አሰመራ አንድትልክ። እዚህ የሚቀሩትን እኔ በሚቀጥለው ሳምንት መጥቼ አያቸዋለሁ። ምንም ዓይነት አቤቱታ መሰማት አልፈልግም። የሚያስፈልጋቸው ሁሉ መሟላት አለበት። ችግር ካለብህ ጠይቅ! በርቱ!!" ብሎ ወደ መኪናው አመራ።

ወደ ከረን ቀዳሚ መምሪያ ነበር የተመለስነው። ከመኪኖቹ አንደ ወረድን ጀ/ደምሴ ወደ ዘመቻ መምሪያው የጦርነቱን ሁኔታዎች ለማጣራት ገባ። እኔም ባየሁት ሁሉ ግራ መጋባት ሰውነቴን አጥለቅልቆት ስለማንነቴ፤ ለምን እንደ ተፈጠርኩ፤ ለምን ለባዶ ተራራ እንደምንዋጋ ብዙ ዓይነት ጥያቄ በአንጎሌ ይመላለስ ጀመር። 'ለምን ለአንድ ባዶ ተራራ እንዋጋለን? ለምን ይሄ ሁሉ ሰው ያልቃል፣ ይቆሰላል፣ ይሰቃያል?'

አባቴ ከዘመቻው ቢሮ ምንም ስሜት ሳያሳይ ወጣና በረንዳው ላይ ጎርደድ ማለት ጀመረ።

"እንዴት ነው ጦርነቱ?" አልኩኝ ጠጋ ብዬ ስለሁኔታው ለማወቅ ከነበረኝ ጉጉት የተነሳ ሲነጋገሩ ለመስማት መጠበቅ አቃተኝ።

"ያህና ነው። መጀመሪያው ቦታው ላይ የነበሩት በአብዛኛው ተደምስሰዋል። ነገር ግን ተጨማሪ ኃይል ማምሻውን አንቀሳቅሰው አምጥተው መልሰው ለማጥቃት ይሞክራሉ። እኛም ተዘጋጅተን እንጠብቃቸዋለና?" አለና ፈገግ አለ።

እኔም አብሬ ፈገግ አልኩ። ቀድሞ እንደ ተሰማኝ ስሜት ከፈገግታ ጋር ለዕድሜ ልክ የተሰነባበትን መስሎኝ ነበር። ሕይወት ግን ሳሙና ማለት ናት። ሙለጭልጭ፤ እንደ አሰስት የምትቀያየር። ጭራዋ የማይያዝ ሙልጭልጭ ሕይወት።

ቀዳሚው መምሪያውን ለቀን ከተወሰኑ መኮንኖች ጋር ወደ ከረን ሆቴል ሄድን። እራት ለመብላት አንድ አዳራሽ ውስጥ ገባን።

"ጌታሁን እንግዲህ አልጋ እዚህ ለሁሉም እንዲዘጋጅ አድርግ!" አለ ጀ/ደምሴ ልዩ ፀሐፊውን እየተመለከተ።

"አሺ ጌታዬ" ብሎ ተነስቶ ሲወጣ እኔም ሆቴሉን ለመመልከት ተከትዬው ወጣሁ። ወደ መመዝገቢያው ነበር በቀጥታ ያመራው።

"ሠላም እንደምናችሁ! ሰባት አልጋ እንዲዘጋጅ እንድትነግሩልን ነበር።" አለ ሻ/ጌታሁን።

"ሰባት አልጋ ቀርቶ አንድ አልጋ የለም" አለ ከጠረጴዛው ጀርባ የተቀመጠው የሆቴሉ ባለስልጣን ብጤ።

"የተግባባን አልመሰለኝም። በዚህ ሆቴል ያሉትን ሲቪል አንግዶች ወደ ሌላ ሆቴል ማዛወር አለባችሁ። ከአስመራ ለሥራ የመጡ አንግዶች አሉን። እዚህ ነው የሚያርፉት። ወጪአችሁ ሁሉ ይሸፈናል።" አለ ሻ/ጌታሁን ረጋ ብሎ።

"ይሄማ ጨርሶ የማይሆን ነው። ሆቴሉ በሙሉ ተይዟል" አለ ሰውዬው በሁኔታው እየተገረመ አትቀልድ በማለት አኳኋን።

"ወንድም ካንተ ጋር ጊዜ አላጠፋም። ከሥራ አስኪያጁ ጋር አገናኘኝ"

"ገብተው ያነጋግሯቸው፤ የሚመጣ ለውጥ ያለ አይመስለኝም"

ሻ/ጌታሁን ሥራ አስኪያጁን አነጋግሮ ወጣና

"በል አልጋዎቹ በፍጥነት አንዲዘጋጁ አድርግ" ብሎት አለፈ። እኔም ተከተልኩት።

ከአራት በኋላ ወደ መኝታ ክፍላችን ስንሄድ የከረን ሆቴል በወታደሮች እና በብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ተከባ ነበር። ፎቅ ላይ ያለችው ክፍል ለአባቴና ለእኔ ነበር የተያዘችው። መታጠቢያ ክፍል ገላዬን ለመታጠብ ብገባ ውሃ ሰላጣሁ ወደ አልጋዬ ገብቼ ተኛሁ። እንቅልፍ ፍለጋ ስገላበጥ በሌሊቱ ፀጥታ ውስጥ አልፎ አልፎ የመድፍ ድምፅ መሰማት ጀመረ። ድምፁ በጣም በትንሹ ድም! ድም! ድም! ሲል ቀን የነበረው ትርኢት ሁሉ በአንጎሌ መጣና ተደነቀረ። የመድፉን ድምፅ አያዳመጥኩ የተፋፋመ የጦርነት ሕልም ውስጥ ገባሁ።

ከጥዋቱ ወደ ሰድስት ሰዓት ገደማ ከአልጋዬ ላይ ገልበጥ ሰል አባቴ የተኛበት አልጋ ባዶ መሆኑን በጨረፍታ ተመለከትኩ። በቅጽበት ከአልጋዬ ተስፈንጥሬ ልብሴን ለበስኩና ወደ በረንዳው ወጣሁ። እዚያም ማንም

የለም። የመኝታ ቤቱን በር ከፍቼ ሰወጣ አንድ የወታደር ፓሊስ ፊት ለፊት ወንበር ላይ ተቀምጦ አየሁት።

"የት ሄዱ?" አልኩት

"አሳቸው ሌሊት ነው ወደ መምሪያ የሄዱት። የተቀሩት እዚህ ናቸው። ታች መትረየሶች ይጠብቁሃል።" አለኝ። መትረየስ የተጠመደበት ዋዝ ጂፕ ላይ ያሉትን ወታደሮችን ማለቱ እንደሆነ ገባኝ። "እሺ አመሰግናለሁ። ደህና ሁን" ብዬ ወደ ታች ወረድኩ።

መውጫውን ከፍቼ ሰወጣ መትረየስ የተጠመደበት ግልጽ ዋዝ ቆሟል። ሠላምታ ተለዋወጥንና ዋዙ ላይ ከኋላ ተሳፍሬ ወደ ቀዳሚ መምሪያው በረርን። የወታደር ዝጉርጉሩን የጦርሜዳ ልብስ ለብሼ ስለነበር፤ ወታደሮቹ ማንነቴ የገባቸው አልመሰለኝም። እኔም ዝም ብዬ ሠላምታ ሲሰጡኝ በወታደር ደንብ ሠላምታ አመልስ ነበር። ቀዳሚ መምሪያው ስንደርስ ጀ/ደምሴና ረዳቶቹ ጀ/ታደሰ ከሚገኙበት የከረን ተራራ ምሽግ መሄዳቸው ተነገረንና ወደዛው ቀጠልን። እዚያ ስንደርስ ከቀድሞዋ ቅጠል መሰል ድንኳን ሥር ተቀምጠው ጠበቁን።

"እህስ ልጅ ደረጀ ብደንብ ተኛህ?"

"እዎን በደንብ ተኛሁ። ጥዋት ሳጣህ ብቻ ትንሽ ደነገጥኩ። ስትሄድ ብትቀሰቅሰኝ ጥሩ ነበር"

"አይ አንድትተኛ ብዬ ነው። እኔ ያንን የመድፍ ድምፅ አያዳመጥኩ ሆቴል ቤት መተኛት አልቻልኩም። እዚያው ቀዳሚ መምሪያ በሬዲዮ ኮንታክት

እያደረኩ አነጋሁ" ብሎ ቀጠለና "ታዲያ ወደ አስመራ ከመመለሳችን በፊት ከረንን ዞር ዞር አድርገው ያሳዩሃ?" አለኝ።

"እሺ በጣም ደስ ይለኛል"

"ጌታሁን ዞር ዞር በሉና ኑ"

"እሺ ጌታዬ"

የተሸፈነችዋ ዋዝ ውስጥ ገባሁና መንገድ ስንጀምር መትረየስ የተጫነበትም ዋዝ ተከተለን። የከረንን ከተማ በዝግታ እየተዘዋወርን ዋናው ገበያ ደረሰን። የጠፈ የአርዳታ እህል ንግድ ተሟጥፏል። ግመል የሚጎትቱ ነጭ ጥምጣም የጠመጠሙ ነጋዴዎች ገበያዋን አጣበውታል። በገበያው ዞርንና አንድ የወታደር ተቋም ውስጥ ለመግባት ከበሩ ቆምን። በከረን የሚገኝ የጠሩ ዳቦ ቤት ነበር። በጣም ትልቅ ግቢ ነው። የይለፍ ቁጥር ስንጠየቅ ስላልነበረን ጭቅጭቅ ሳንፈጥር ተመለስን። በየመንገዱ የሚዘዋወረው ወታደር ሠላምታ ሲሰጠን አባቴ እንደሚያደርገው ሁሉ በወታደር ደንብ ሠላምታ እየመለስኩ ወደ ተራራዋ ተመለስን።

ከመኪናዋ ወርጄ ወደ ድንኳኗ ሰጠጋ "አዎ ልክ አይደለም አኛ እነሱን ኢትዮጵያውያን ናችሁ እያልን እንደገና የወንበዴ ሬሳ አናነሳም ማለት ጨርሶ ልክ አይደለም። ለሁሉም ግንባር ትዕዛዝ አስተላልፏል። ሬሳ የተባለ ጊዜ አያላቸው ሳያነሱ እንዳያልፉ" የሚል የጂ/ደምሴ ድምፅ ሰማሁና ያየኋቸው ሰዎች በሃሳቤ መጥተው የጥዋቱ ንጹህ አየር ያደሰው ሰሜቴ እንደ መደፍረስ አለ።

ጂ/ደምሴ የሬዲዮ መልእክቱን ጨርሶ ጂ/ታደሰን ከተሰናበተ በኋላ ወደ አስመራ ለመመለስ ወደ አየር ማረፊያ አመራን። በመንገዳችን ላይ "ሌሊቱን ሙሉ መልሶ ማጥቃት ሲያደርጉ ነው ያደሩት። እንደ ሌላው ጊዜ ጠሩ ተዝረክርኮ የሚጠብቃቸው መስሏቸው ነበር። አንጀታቸው ነው የደበነው። ብዙ ሰው ነው ደግሞ ያለቀባቸው። ጠሩም ትንሽ ድል እያገኘ ሲሄድ ሞራሉ ይገነባል።" አለ፣ አሁንም ማናችንንም ሳይመለከት።

ከረን አየር ማረፊያ ስንደርስ ሄሊኮፕተሯ ገና በማረፍ ላይ ነበረች። ከረን አብረውን የተዘዋወሩትን መኮንኖች ስንሰነባበት ጂ/ደምሴ ራቅ ብሎ የቆመውን አንቡላንስ ተመለከተና

"ቁሰለኞች አሉ እንዴ?" ብለው ጠየቁ።

"አዎን ጌታዬ በሚቀጥለው ሄሊኮፕተር ይሄዳሉ ብለን ነው።"

"ለምን? በሉ ጥሯቸውና በፍጥነት ይጫኑ።" አሉ። ቁሰለኞቹ በሄሊኮፕተሯ ወለል ላይ ቃሬዛ ተዘርግቶ በረድፍ ከተኙ በኋላ እኛ ገብተን ቦታችንን ያዝን። እነዚህ ቁሰለኞች "አስጊ ሁኔታ ላይ ናቸው" የተባሉና ከባድ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ናቸው። የጉሉኮስ ፍሳሽ እየወሰዱ ስለነበር ማንጠልጠያ ባለመኖሩ ግሉኮሱን ከፍ አርገን መያዝ ነበረብን። ፊኛቸውን መቆጣጠር በማይችሉበት ደረጃ ላይ ስለነበሩ ከወገባቸው በታች አርቃነ ሥጋቸውን ቱቦ መሳዩ ላስቲክ በየብልታቸው ገብቶ ለሚያያቸው አንጀት ይበላሉ። ከመህላቸው አንደኛው አለመጠን ይወራጭ ስለነበርና አጠገቡ የተኛውን ቁሰለኛ የተጎዳበትን አካባቢ እየነካ ስላስቸገረው አንድ መኮንን የጫማውን ክር ፈቶ የሚወራጨውን ቁሰለኛ አግር ከሌላኛው አግሩ ጋር

አላልቶ አሰረው። ጣር ይዞት የሚወራጨው ቁስለኛ አስመራ አየር ማረፊያ ስንደርስ ለዘላለም ተለየን።

አስመራ አየር ማረፊያ ቁስለኛ ለመውሰድ የተሰለፉት አምቡላንሶች እንደቆምን ተንደርድረው መጡና በክፍተኛ ፍጥነት ቁስለኞቹን አየጫኑ ወሰዷቸው።

አስመራ እንደ ደረስን የሰሞኑን ድካም በውሃ አወጣው ይመስል ረዘም ላለ ጊዜ ገላዬን ታጥቤ ወደ መስሪያ ቤቴ የአስመራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሄድኩ። ከመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ጋር ትንሽ ከተጨዋወትን በኋላ ሻዕቢያ ያቃጠላቸውን አሰራ አምስት አህል ጭነው ይጓዙ የነበሩትን የተባበሩት መንግስታት ጭነት መኪኖችን ከተቃጠለው ሰንዴያቸው ጋር ተመልክቼ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።

ማምሻዬን ያለፉትን ቀናት ትዝታ ካንጎሌ ለማራቅ አንዲ መጽሐፍ ሳነብ አንዲ ሬዲዮ ሳዳምጥ አባቴ ከሥራ መጣ።

"ታዲያስ ጦርነቱ እንዴት ነው?" አልኩኝ አሁንም ለመስማት ጓጉቼ

"አሁን ከተራራው አካባቢ እያራቅናቸው ነው። የሚቀጥለው ተራራ ላይ ለመመሽግ አየሞከሩ ነው። ምን አባክህ ጦርነት እኮ አሸናፊ የለውም። እነዛን ቁስለኞች አላየህም። በዚህ ጦርነት ብዙ ሰው አልቋል። እና ዝም ብለን በዚህ ሁኔታ መቀጠል አንችልም። እንዳናሸንፍ ያደረጉን መሠረታዊ ችግሮች አሉ። ዝም ብሎ በጦርነት የሚሆን ነገር የለም፣ ዋናው እንድታይ የፈለግኩት ይሄን ነው።"

"በጦርነት አንድናሸንፍ ከተፈለገ ደግሞ አንደዚህ አይደለም። ብቃት ያለው ጦር አሰልጥነን የተሟላ ትጥቅ አስታጥቀን። ምግብ፣ ውሃ፣ ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮች ተሟልተው፣ ወታደር በግድ ሳይመለመል... የአስር ዓመት ሠላም ኖሮን ዝግጅት ማድረግ ብንችል በእውነት ጦርነቱ በወራቶች ውስጥ ያልቅ ነበር። አሁንም ቢሆን እኛ ማድረግ ያለብን ለማንኛውም ድርድር የበላይነት የሚሰጠንን ያህል መሬት መያዝና አንድ ዓይነት መፍትሄ መፈለግ ነው። እንዲሁ እየተዋጉ መኖር ይቻላል። አሁን ባለን ጦር ግን ጦርነቱን እንጨርሳለን ማለት ዘበት ነው" አለኝና ቀጥሎ

"አሁን ትግራይን አለምንም ስትራቴጂ አጸዳን ሲሉ ቆይተው፣ እነ አምሳ አለቃ ለገሠ በሠራዊቱ ላይ ቀለዱበት። መሬት መያዝ አይደለም ቁምነገሩ፣ ታርጌታችን መሬት ሳይሆን ወንበዴው መሆን አለበት ብንል ሲሰሙን አልቻሉም። አንድ አሰር ሰው መርቶ የማያውቅ ሃምሳ ዓለቃ የሠራዊት አዛዥ ሲሆን ምን ትላለህ? ብዙ ችግር አለ...! ይቺ አገር ምን ቁጣ አንደ ወረደባት አይገባኝም።" አለኝ።

ወዲያው ደግሞ ከፍቶት የነበረውን ፊቱን ፈካ አድርጎ "በል ወንድሜ፣ ወደ መኝታ እንሂድ። ከንገወዲያ ነው የምመለሰው አልከኝ?" አለኝ።

"አዎን እንደዚያ ነው ያሰብኩት"

"እኔ ነገ ወደ ግንባር መሄዴ ነው። እንግዲህ እዚያ አንድ ሁለት ቀን መቆየቴ አይቀርም እና የምንገናኝ አይመስለኝም ልሰናበትህ?" አለኝና እጁን ዘርግቶ ተጠጋኝ። ተቃቅፈን ተሰነባበትን ከአባቴ ጋር። "በል እንግዲህ በርታ

ብዙ ትምህርት አንዳገኘህ ተስፋ አለኝ" አለና በፍቅር ዓይን ፈገግ ብሎ ተመለከተኝ።

"አዎ ብዙ ትምህርት ነው ያገኘሁት። አንተም አንግዲህ ራስህን ጠብቅ ስለኛ አታስብ።" አልኩና ከቀምኩበት ሳልንቀሳቀስ ቀረሁ።


"እይዞህ አታስብ ምን አሆናለሁ ብለህ? በል ሂድ ተኛ" አለና አንደገና አቅፎ ሰሞ ተሰናበተኝ።

የመኝታ ቤቴን ግድግዳ እያየሁ ሌሊቱን አጋመስኩና እየተከታተሉ የሚመጡብኝን ሃሳቦች አንደ ማራገፍ ሁሉ ተገላበጥኩና ተጠቅልዬ ተኛሁ።

ጥዋት ሰነሳ አባቴ አልነበረም። እቃየን ጠቅልዬ ከባሻ ክፈተው ጋር ወደ አየር ማረፊያ ብሄድ፣ አውሮፕላኑ ጥዋት በ6 ሠዓት እንደለቀቀ ተነገረኝ። በሁኔታው ተገርሜ ቀጠሮ የሠጠኝን ሰርጂዎ የሚባለውን ጣሊያናዊ ብጠይቀው፣ እንደመቀለድ ብሎ "ተሳስቼ ነው በከነባ ወዲያው ትሄዳለህ" ብሎኝ ቁጭ አለ። በሁለተኛው ቀን አባቴ ሲመለሥ ከወትሮው የተለየ ብርሃን ፊቱ ላይ ይታይ ነበር። ፈገግ አለና "ታዲያስ? አንተ ወዳጀ ናቸው እያልክ የምትፎክርባቸው ሰዎች ጉድ አደረጉህ አይደል?!" አለኝ። አሁንም እጁን ዘርግቶ እያቀፈኝ። መቅረቴን ነግረውት ስለነበር ሲያየኝ አልተገረመም።

"ምን እባክህ ሰውዬው ይቀልዳል። ተሳስቼ ነው አለኝ እኮ። ነገ ጥዋት ሌላ አለ ብሎኛል" አልኩት ከተሳሳምን በኋላ።

"አንተ ጨርሶ ሊገባህ ያልቻለው ነገር ፈረንጆች ለኛ ለጥቁር ሕዝቦች ምንም ዓይነት አክብሮት አንደ ሌላቸው ነው። ያውም ጣሊያን? ትናንትና



U.S.N.S. GENERAL R. M. BLATCHFORD (T-AP153)

የከብር ዘበኛን ቃናው ሻለቃ ወደ ኮሪያ ይዞ የተጓዘው ሚከብ



በከብር ዘበኛ እጩ መኮንኖች ኮርስ ላይ

ብዙ ትምህርት አንዳገኘህ ተስፋ አለኝ" አለና በፍቅር ዓይን ፈገግ ብሎ ተመለከተኝ።

"አዎ ብዙ ትምህርት ነው ያገኘሁት። አንተም አንግዲህ ራስህን ጠብቅ ስለኛ አታስብ።" አልኩና ከቆምኩበት ሳልንቀሳቀስ ቀረሁ።


"አይዞህ አታስብ ምን አሆናለሁ ብለህ? በል ሂድ ተኛ" አለና አንደገና አቅፎ ሰም ተሰናበተኝ።

የመኝታ ቤቴን ግድግዳ እያየሁ ሌሊቱን አጋመስኩና አየተከታተሉ የሚመጡብኝን ሃሳቦች አንደ ማራገፍ ሁሉ ተገላበጥኩና ተጠቅልዬ ተኛሁ።

ጥዋት ስነሳ አባቴ አልነበረም። እቃየን ጠቅልዬ ከባሻ ክፈተው ጋር ወደ አየር ማረፊያ ብሄድ፣ አውሮፕላኑ ጥዋት በ6 ሠዓት እንደለቀቀ ተነገረኝ። በሁኔታው ተገርሜ ቀጠሮ የሠጠኝን ሰርጂዎ የሚባለውን ጣሊያናዊ ብጠይቀው፣ እንደመቀለድ ብሎ "ተሳስቼ ነው በከነባ ወዲያው ትሄዳለህ" ብሎኝ ቁጭ አለ። በሁለተኛው ቀን አባቴ ሲመለሥ ከወትሮው የተለየ ብርሃን ፊቱ ላይ ይታይ ነበር። ፈገግ አለና "ታዲያስ? አንተ ወዳጂ ናቸው እያልክ የምትፎክርባቸው ሰዎች ጉድ አደረጉህ አይደል?!" አለኝ። አሁንም እጁን ዘርግቶ እያቀፈኝ። መቅረቴን ነግረውት ስለነበር ሲያየኝ አልተገረመም።


"ምን አባክህ ሰውዬው ይቀልዳል። ተሳስቼ ነው አለኝ እኮ። ነገ ጥዋት ሌላ አለ ብሎኛል" አልኩት ከተሳሳምን በኋላ።

"አንተ ጨርሰ ሊገባህ ያልቻለው ነገር ፈረንጆች ለኛ ለጥቁር ሕዝቦች ምንም ዓይነት አክብሮት አንደ ሌላቸው ነው። ያውም ጣሊያን? ትናንትና




U.S.N.S. GENERAL R. M. BLATCHFORD (T-AP153)


የክብር ዘበኛን ቃኘው ሻለቃ ወደ ኮሪያ ይዞ የተጓዘው ሚከብ




በክብር ዘበኛ እጩ መኮንኖች ኮርስ ላይ



መ/አ/ደምሴ እና መ/አ//አስራት ብሩ በአሜሪካ ፎርት ቤኒንግ፣ ጆርጂያ- 1951



መ/አለቃ ደምሴ በበረዶ በተሸፈነው ተራራ ላይ- ኮርያ በኢትዮጵያ -1947




ጄኔራል ደምሴና የእስራኤል አየር ወለድ መኮንን በአንድ ሥልጠና ላይ



በአሜሪካ ሥልጠና ላይ




ሻምበል ደምሴ ከባለቤታቸው
ከወ/ሮ አስቴር አዳሙ ጋር



ለመጀመሪያ ጊዜ ለሥልጠና የተላከወዓ ጦር
ሞተው እስራኤል አገር በመሄድ
የኢትዮጵያን አየር ወለድ ያቋቋመት ሶስቱ
መኮንኖች፣
መ/አ እስጢፋኖስ ገ/ሚካል መ/አ አስራት
ብሩ እና መ/አ ደምሴ ቡልቶ



ሻለቃ ደምሴ እና ወ/ሮ አስቴር አዳሙ
1963 ካንሳስ – አሜሪካ




የአየር ወለድና የባህር ኃይል መኮንኖች ጦሞራ ልምምድ ጊዜ
ምጽዋ : 1959




የአየር ወለድ አዛዥ ኮለኔል ጌታቸው ናደው ሻለቃ የዓለምዝወድና ረዳት መኮንኖቻቸው ጋር በቀኝ
በኩል ሁለተኛው ለግብጥ የተሰሩት ጀነራል ተፈሪ ባንቲ ናቸው። ከተቀማጩ በወቅቱ ሻምበል ደምሴ
በልቶ፡ ሻምበል እስቲፋኖስ ገ/ሚካል : መቶ/አ ደምሴ ደረሳ፡ ከቆመት መቶ/አ ሰይፉ ወልዴ
: መቶ/አ እባተ ሞሻ : መቶ/አ ሽባባው ዘለቀ ይገኙበታል፡



የሐረር አካዳሚ ምረቃ ሥነስርዓት ላይ ከግራ ወደ ቀኝ የሱዳኑ ሜ፣ አዜ ኃ/ሥላሴ፣ ሚ/ጄነራል ግዛው በላይነህና ሌ/ኮ ደምሴ በልቶ



የሐረር አካዳሚ ምረቃ በዓል ላይ




THE COMMANDANT, OFFICERS & PROFESSORS Neh 1961 (Aug 69)

የሐረር ጦር አካዳሚ አዛዥና አስተማሪዎች



ሮኔራል ደምሴ ከከብው ጄነራል አቾዋ ጋር



ሌ/ኮ ደምሴ ከሻምበል ተስፋዬ ትርፌ እና ከሐረር አካዳሚ መኮንኖች ጋር ለሚከለከሉ




ሻ/ ደምሴ ና መ/አ/ተስፋዬ ትርፌ ከሕንድ መኮንኖች ጋር ሕንድ አገር በትምህርት ላይ



ሻ/ደምሴ በፐብሊክ
አድምንስትሬሽን
ዲፕሎማ ሲሚቁ የተነሱት



ሻ/ደምሴ አሜሪካ የሚገኘዉ የዌስት ፖይንት መኮንኖች ሚከለከሉ ሚከል- በጉብኝት ላይ - 1963




ከአርሚ ጀነራል ስታፍ ኤንድ ኮማንድ ኮሌጅ ሲሚቁ



ጀነራል ደምሴ ከረዳት መኮንናቸው ከሻ/ጌታሁን ጋር የ10ኛ ክ/ጦርን በመጎብኘት ላይ (ሻ/ጌታሁን ከኋላቸው ጃኬት ለብሰው የሚቆቱት ናቸው)



ኮለኔል ደምሴ የደቡብ ዕዝ አዛዥ በነበሩበት ጊዜ በሲዳሞ ክ/ሐገር የኢትዮጵያ ጠረፍ አካባቢ የተነሱት ፡ በስተቀኝ ሻለቃ በረታ ኀሞራው (ብ/ጀነራል ይደረሱ)






ሜ/ጀ ደምሴ የጦር ሜዳ ማዘራሪያ ሲቀበሉ
ሻ/ጌታሁን ል/ዩ ረዳት (ኤዲሲ) ከኋላቸው የቆሙት ናቸው



ጀኔራል ደምሴ ለጦር ሜዳዎች መሚያ ሲሰጡ



በአጋዴን የጦር ጉብኝት ላይ ጀኔራል ሞዕድ ጄ/ደምሴ እና ጀ/ወርቁ ቸርነት በተከታታይ ከሐሊኮፕተር እንደወረዱ የተነሳ



ጀ/ደምሴ የጦር ሜዳ ካርታ እያጣኑ ትዕዛዝ ሲሰጡ



ጀ/ደምሴ ቁስለኞችን በማጽናት ላይ- ማጽራቸውን ይዘው የቆሙት ጀ/ር ወርቁ ቸርነት ናቸው




በኢትዮጵያ የሚጠሉጥኑትን የሶሜኒ ነጻ አወጪ ጦር የሚደርገው ዒላማ ልምምድ ሲጎበኙ



የተቃጠለ የሶሜሌ ታንክ




ጀራኔራል ደምሴ የሩሲያ ጀነራሎችን ሲያነጋግሩ



ከሱሜሌ የተሚረከ የጦር መሣሪያ




ጀ/ደምሴ እና ጀ/ሞሪዕድ ገለጻ ሲሰሙ



ሐረር የነበረው የአንደኛ ሠራዊት ምክረታ የአሰረኛ ዓመት በዓል ላይ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ጄ/ኃይለጊዮርጊስ ለጀ/ደምሴ- ላደረጉት
አስተዋጽ አ የሠራዊቱን አርማ ሲሰጧ አጠባቸው የቆመት ከግራ ወደቀኝ የሠራዊቱን አዛዥነት የተረከቡት ጀኔራል አበራ አበበ እና ም/ አዛዡ ጀነራል ጌታቸው ገዳሙ ናቸው። በ1981 ደርግን ለመጣል
በተደረገው እንቅስቃሴ ጄ/ኃይለጊዮርጊስ በጀኔራል አበራ ተገድለዋል።



አቶ በልቶ ኤጀርሳ ከልጃቸው ጀነራል ደምሴ ጋር



ጀነራል ደምሴ ቡልቶ አስሚራ 1980



ከአባቴ ጋር

ሕዝባችንን ሲጨርስ ከርሞ ዛሬ ለኛ መጓጓ ፈቃጅ ሆኗል። በል ወንድሜ በሆው አየር መንገድ ትሄዳለህ። ትኬት እንዲቆርጥሉህ አነግርልሃለሁ።" አለኝ "ግድ የለም የነገውን ልየውና ባይሆን ከዚያ በኋላ በአየር መንገድ እሄዳለሁ"

"በል እንደፈለክ። ብቻ ፈረንጆቹን ብዙ አትመናቸው።" አለኝና ከሶፋው ላይ ተተምጠ አንዱን ሰልክ አነሳ።

ጣቶ አራት ከበላን በኋላ "በል እንግዲህ በድጋሚ መልካም ጉዞ- በርታ!" አለና አቅፎ ተሰናበተኝና ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ።

እኔም ከዚያ ግድግዳ ጋር እንደገና ለመፋጠጥ ወደ መኝታ ቤቱ ገብቼ በሩን ዘጋሁ።

አባቴን ከዚያ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ ለሁለት ሳምንት የመጣ ጊዜ ነበር። ያቺ ጊዜ ከአባቴ ጋር ያሳለፍኳት የመጨረሻ ሁለት ሳምንት ነበረች።

-10-

ከልጅነት ወደ መኰንንነት

አቶ ቡልቶ ኤጀርሳ ከአድዋ አውራጃ ከደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ ጋር ማይጨው ዘምተው ከጣሊያን ወራሪ ጦር ጋር ሲዋጉ ከዚያ በፊት አይተው በማያውቁት ዘመናዊ መሣሪያና የአውሮኘላን ቦምብ ድብዳባ ብዙ ጓደኞቻቸውን አጥተው ነበር። እርሳቸውና አብሯቸው የነበረው የኢትዮጵያ አርበኛ ወኔ ሳያንሰው በዘመናዊ መሣሪያ አጥረት ጠላቱን መልሶ የመምታት እንኳን አድል አላገኘም። ከአየር እየተዝዋዋደዱደ በሚወርድ ቦንብ እየተመታ ሲወድቅ ያዩት ሁሉ ከአምሮቸው ሊወጣ አልቻለም። አግዚአብሔር ከነሕይወታቸው አገራቸው ከመለሳቸው አንድ በአሳቸው ጊዜ ብዙ ሰው የማያስበውን ውሳኔ ለመውሰድ ለራሳቸው ቃል ገቡ። ይህም ውሳኔ ልጆቻቸውን አዚያው የትውልድ አገራቸው አድአ በርጋ መሬት ሰጥተው የንብረታቸው አስተዳዳሪ ከማድረግ ይልቅ ወደ አዲስ አበባ ልከው ዘመናዊ ትምሕርት ለማስተማር ነበር።

"ልጅቼ ጣልያን ተመራምሮ የደረሰበትን ተምረው እንዲደርሱበት አስተምራለሁ" ብለው ወሰኑ። በዚያን ጊዜ፣ ከአድአ በርጋ፣ ልጅቼን ወደ አዲስ አበባ ልኮ ያስተማረ ሌላ ባላባት አልነበረም። አባባ ቡልቶ

ልጆቻቸውን በዚሁ ውሳኔ መሠረት አስተምረው፣ አንድ የገንዘብ ሚ/ር ሠራተኛ፣ አንድ ሜጀር ጀነራል፣ አንድ የፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ ፣አንድ የሕክምና ዶክተር፣ አንድ የክፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ አፍርተዋል። አባቴ ሜጀር ጀነራል ደምሴ ቡልቶ በ1926 ዓም የተወለደው ሶስተኛው ልጃቸው ነበር።

አድአ በርጋ ከሙገር ሰሚንቶ ፋብሪካ በፈረስ ወደ ሶስት ሰዓት መንገድ ርቀት ላይ ያለች ከቢላቻ ወንዝና ፎየታ ተራራ በስተጀርባ የምትገኝ ቦታ ናት። አያቴ የሚኖሩበት አነስተኛ ተራራ አናት ላይ ከጥቂት ቤቶች በስተቀር ሌላ የመንደር ምልክቶች አንኳን የሉበትም። አቶ ቡልቶ ብዙ ጋሻ መሬት እና ጥቂት ሠራተኞች ነበሯቸው።

ሲባል እንደምሰማው፣ አባቴ በልጅነቱ ጠባዩ ቅብጥብጥና ውሃ ቀጠነ ብሎ ከሁሉ የሚጣላ በጥባጭ ነበር። አያቴ ቤት ከነበሩት መድሀኔ የሚባሉ እሮጊት "ቅስቅሶ ብጥብጥ" (በጥባጭ ቆስቋሽ) ብለው ሰም አውጥተውለት ነበር። ጦር፣ ዱላ፣ ወይም አንካሴ ሳይዝ ከቤት አይወጣም። ብዙ ጊዜ በእነዚህ መሣሪያዎች አውሬ ሲያድን ይውላል። አልኽኛ ስለነበር ሲቆጣ በማባበል አንጂ በኃይል አይመለስም። ፈረስ ግልቢያ ይወድ ስለነበርና የሚጋልበውም ፈረስ ስም "ዳኘው" ስለነበር ያገሩ ሰው "አባ ዳኛው" ብሎ ይጠራው ነበር።

ያደገበት ቋንቋ ኦሮምኛ ስለነበር እድሜው ለትምሕርት ሲደርስ አባቱ የእማርኛ መምሕር ቀጥረው ከወንድሞቹና ከጐረቤት ልጆች ጋር እንዲማር አደረጉ። የተቀጠረው አስተማሪ አገር ለቆ ሲሄድ ታላቅ ወንድሙ አስተማሪ ወደሚገኝበት ሲላክ እርሱ ግን ርቆ ሄዶ ለመማር ገና ነው ተብሎ እንዲቆይ ተወሰነ። እሱ ግን አሻፈረኝ አለና አንድ ቀን በራሱ ሃይል ከወንድሙ ጋር ሮጠ ተቀላቀለና ኢንጭኒ ጊዮርጊስ ት/ቤት ገባ። ኢንጭኒ ጊዮርጊስ ድረስ የበሰለ ምግብ፣ በእናቱ ወ/ሮ አዬ ጅራኔ ጥብቅ ክትትል እየተዘጋጀ፣ አቶ ዱባስ በተባሉ ታማኝ አገልጋይ በኩል እየተላከለት ከወንድሙ ጋር ትምሕርቱን ቀጠለ። በቤተክርስቲያን ትምህርት አሰጣጥ መሠረት ዳዊት ደግሞ፣ የውዳሴ ማርያምን እና የዜማ ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ፣ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ በጊዜው ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ግብጻዊ አቡነ ቄርሎስ የድቁና ማዕረግ ተቀብሏል።

አቶ ቡልቶ ለራሳቸው ቃል በገቡት መሠረት አባቴንና ወንድሞቹን አዲስ አበባ ዘመናዊ ት/ቤት በጊዜው የባላባት ት/ቤት በመባል ወደሚታወቀው የመድሐኒያለም ት/ቤት አስገቡ። አዬ ጋይለ ሥላሴ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሐገሮች ባላባቶች ልጆቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ልከው እንዲያስተምሩ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ስለነበር፣ ከየቦታው የመጡት ተማሪዎች በብዛት መድሐኔዓለም ት/ቤት ነበር የሚማሩት። ሰሙም የባላባት ት/ቤት የተባለው ለዚህ ነበር።

ከተለያዩ ቦታዎች ከመጡት ተማሪዎች ውስጥ አንዱ ከሐረር የመጣ የሱማሌ ባላባት ልጅ ከአባቴ ጋር መድሐኔ ዓለም ት/ቤት ተምሮ ከብዙ አመታት በኋላ ሶማሊያ ኢትዮጵያን ስትወር እሱ የሶማሌ አየር ኃይል አዛዥ፣ አባቴ ደግሞ የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ሆነው ተዋግተዋል። አባቴ መድሐኔዓለም ት/ቤት ሲገባ አገር ቤት የሚወደውን ጠሩን ይዞ ነበር የገባው። ከመኝታ ቤቱ የማይለየውን ጦር ኮሸታ ሲሰማ ወይንም ከሰዎች ጋር ሲጣላ ይዞ እየወጣ ያስፈራራቸው እንደነበር አብረው የተማሩ ጓደኞቹ አያነሱ ብዙ ጊዜ ይስቃሉ።

በመድሐኔዓለም ት/ቤት እንዳለ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ማሠልጠኛ ት/ቤት፣ ለ3ኛ ጊዜ አጨ መኮንኖችን ለማስልጠን መመልመል መጀመሩን ሰማ። ለወላጆቹ ሳይነግር እድሜውን በአንድ ዓመት ጨምሮ በሚሰጥር መኮንኖች ማሠልጠኛ ማእከል ገባ። በስዊድን መኮንኖች የሚመራው የክብር ዘበኛ መኮንኖች ማሠልጠኛ ከዚያ በፊት ሁለት ኮርስ ብቻ ነበር ያስመረቀው። ይህ ሶስተኛ ኮርስ የመጨረሻው ኮርስ ነበር። ከአባቴ ጋር በአጨ መኮንንነት በሶስተኛ ኮርስ ከገቡት ውስጥ፣ ብዙዎቹ የእድሜ ልክ ጓደኞቹ ሆኑ። ከነዚህ ውስጥ ሜ/ጀ መርዕድ ንጉሤ፣ ኮ/ል አስጥፋኖስ ገብረመስቀል፣ ኮ/ል ግርማ ተሰማ፣ ሜ/ጀ አስራት ብሩ፣ ሜ/ጀ ሙላቱ ነጋሽ ሜ/ጀ ክንፈ ሚካኤል ድንቁ፣ ሜ/ጀ ረጋሳ ጂማ፣ እንዲሁም ቀደም ብለው ከውትድርና የወጡት ጓደኞቹ ሻምበል ጌታቸው ወልደማርያም፣ መ/አ ካሳ ጎይ፣ ሻ/ዘውዴ ወ/ቂርቆስ ና መ/አ በቀለ ሰጉ* ይገኙበታል።

(*መ/አ በቀለ ሰጉ ከከብር ዘበኛ ተመርቀው በአ.አ.ዩኒቨርስቲ የዲግሪ ፕሮግራም ጥናት ላይ እያሉ በመንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ የዩኒቨርስቲውን አንቅስቃሴ ከመሩት አንዱ ነበሩ። ለ13 ዓመት ከ1953- እስከ 1966 ዓም ድረስ ከተሰወሩበት አንድ ቤት ውስጥ ሳይወጡ፣ ቀንና ሌሊት መጽሐፍ ሲያነቡና ሲመራመሩ ኖረው፣ ለውጡ ሲመጣ ከተደበቁበት ወጡ። ከ13 ዓመት በኋላ ነጻነት ቢያገኙም ከጥቂት ዓመት በኋላ በሌ/ኮ መንግሥቱ ኃ/ማርያም መንግሥት ተገድለዋል።)

አባቴ ከጉለሌ ተነስቶ በእግሩ ወደ መድሃኔ ዓለም ት/ቤት ሲጓዝ ሁልጊዜ አያደነቀ የሚያልፋት የወ/ሮ ፈለቀች ዘመናዊ ጠጅ ቤት ነበረች። ያን ጊዜ ጠጅ በፋብሪካ መመረት የተጀመረበት ጊዜ ነበር። በዛች አፋፍ ብጤ ላይ ባለች ጠጅ ቤት ፊት ለፊት ባለው አረንጓዴ ሳር ላይ፣ ሙሉ ኮትና ሱሪ የለበሱ፣ አንዳንዶቹም ተቀምጠው፣ አንዳንዶቹም የተነጠፈ ጨርቅ ላይ ጋለል ብለው፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ጥሬ ሥጋ ሲቆርጡና ጠጁን ሲያንቀሩቁሩ ይታይ ነበር። ሁኔታቸውን እያደነቀ ያልፋል።

አባቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የኪስ ገንዘብ ተከፍሎት ከክብር ዘበኛ መኮንኖች ማሠልጠኛ ለቀን እረፍት ወጣ። ያኔ ታዲያ ሙሉ ልብሱን ገጭ አድርጎ ታላቅ ወንድሙን አቶ በቀለ ቡልቶን እና ታናሽ ወንድሙን ክበበውን ወደዚያች ጠጅ ቤት ይዟቸው ብቅ አለ። ሌሎቹ ሲያደርጉ አንዳየው አርሱም ጋለል ብሎ ከወንድሞቹ ጋር ጥሬ ሥጋውን ሲቆርጥና ጠጁን ሲጐነጭ አመሸ። ወደ ማሠልጠኛ ጣቢያ ሊመለስ ሲነሳ ሁሉም ሞቅ

ብሎአቸው ስለነበር አቤት ሄዶ አድሮ በነጋታው ቢሄድ እንደሚሻል ተሰማሙ። ጠዋት እንደ ምክንያት አድርጐ ለማቅረብ በአናቱ የተፈረመ ደብዳቤ ጽፎ ወደ ማሠልጠኛው ጣቢያ ገባ። "ልጄ ናፍቆኝ ልጠይቀው መጥቼ ናፍቆቴ አልወጣ ብሎኝ ሳዋራው መሸቶበት አቤት አድሯል።" የሚል ደብዳቤ።

ከሰልፍ በኋላ ይህን ደብዳቤ በማስመልከት አንዱ አሰልጣኝ "እንዳንዶቻችሁ ብላችሁ ብላችሁ ከአናታችሁ ደብዳቤ ማጻፍ ጀምራችኋል።" ብሎ አሾፈበት። የሶስት ዓመት የአጭ መኮንን ሥልጠና ጨርሶ፣ ከአጭ መኮንኖች 3ኛ ወጥቶ፣ በክብር ለመመረቅ ሲዘጋጅ፣ ወደ ኮሪያ በአስቸኳይ እንዲዘምቱ ስለተወሰነ የምክትል መቶ አለቃ ማእረጋቸውን ያገኙት ወደ ኮሪያ ይዟቸው በተጓዘው ጀነራል ብላችፈርድ በተባለው መርከብ ላይ ነበር። ዘመኑ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1946 ዓ.ም ነበር። ከኮርያ ከተመለሱ በኋላ ከአባቴ ጋር የተመረቁት ብዙዎቹ ከጀ/ መንግሥቱ ንዋይ ጋር አብራችኋል ተብለው 1953 በአስራት ወይም በጡረታ ሲወገዱ፣ በጦር ውስጥ የቀሩት የተወሰኑ ነበሩ። እሱ ግን ከነበረበት ከክብር ዘበኛ፣ የዘመቻና ትምሕርት ክፍል፣ ኢትዮጵያ የአየር ወለድ ጦር ለማቋቋም አሰባ ለመጀመሪያ ጊዜ ለስልጠና ወደ አሰራኤል አገር ጦር ሰትልክ ፣ ቡድኑን መርተው ከሚሄዱት መኮንኖች አንዱ እንዲሆን ተመርጠ ሄዶ ነበር። በዚህ የተነሳ እዚያው ጦሩ ውስጥ ሊቀር ችሏል።

አሰራኤል አገር ከአባቴ ጋር ከሄዱት መኮንኖች ውስጥ ሜ/ጀ/አሰራት ብሩ፣ ሜ/ጀ አበራ አበበና ኮ/አስጢፋኖስ ገብረመስቀል ይገኙበታል።

ከአሰራሌል አገር በአየር ወለድ ትምሕርት ሠልጥነው ሲመለሱም የመጀመሪያውን የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር ደብረዘይት ላይ አቋቋሙ።

"በራሪ ነብር" ተብሎ የሚጠራው የዚህ ጦር የትምህርትና የዘመቻ ኃላፊ ሆኖ ከሰራ በኋላ በ1955 በኦጋዴን በኩል ሶማሊያ ጦርነት ከፈተች። ለጦርነቱ የዘመተውን የአየር ወለድ ጦር በአዛዥነት መርቶ በሐምሌ ወር 1955 በደገሐቡር አውራጃ አዋሬ ወረዳ ከሶማሌ ጦር ጋር ተዋግቷል።

የአየር ወለድ ጦር በቀልጣፋነት ወደተፈለገበት ተወርውሮ ለመዋጋት ዝግጁ እንዲሆን የሰለጠነ ስለነበር፣ ችግር በተፈጠረበት ቦታ ይላክ ነበር። በ1957 በባሌ ክፍለ ሐገር በሶማሊያ መንግሥት አነሳሽነት የተጀመረ የውንብድና አንቅስቃሴ ለመዋጋት የአየር ወለድ ጦር ሲዘምት አሁንም ጦሩን መርቶ ተዋግቷል።
አባቴ በደገሐቡር ጦርነት በመጀመሪያ ውጊያ ላይ የሞቱትን አምስት የአየር ወለድ ወታደሮች አስከሬን፣ ደብረ ዘይት ካልሆነ የትም አይቀበሩም ብሎ የትሪንስፖርት እርዳታ ለመጠየቅ በጊዜው የ3ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ወደነበሩት ጀ/አበበ ገመዳ ጋር ቀረበ።

ለጀነራሉ በአየር ወለድ ሕግ እና ደንብ የቀብሩ ሥነስርዓት ደብረዘይት መደረግ እንዳለበት አስረድቶ፣ የአምስቱ አስከሬን በአውሮኘላን ወደ ደብረዘይት እንዲላክ ጠየቀ። ከብዙ ማቅማማት በኋላ ጀነራል አበበ

ፈቅደው፣ የአምስቱ አስከሬን ወደ ደብረዘይት በአውሮኘላን ተልኮ የደብረዘይት ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ቀበራቸው።

ይህን ዜና አዲስ አበባ ያሉ የጦር የበላይ አዛዦች ሲሰሙ "እንዲት ለአየር ወለድ ወታደሮች ከሌሎች የተለየ ይደረጋል። ይህ በጠሩ ውስጥ ብዙ ችግር የሚፈጥር ነው" ብለው ጀ/አበበን ስለገሰጿቸው አባቴን ተክተው የዘመተው የአየር ወለድ ጦር አዛዥ ሆነው የለሄዱትን ሻ/አስጢፋኖስን ጀ/አበበ "ያ ጓደኛህ አታሎ አሰወቀሰኝ አይደል?" ብለው አሉዋቸው። አባቴ ከብዙ ዓመት በኋላ በኤርትራ ከርከበት ላይ የተሰውትን የብ/ጀ/ተመስገንን አስከሬን ጦር ሜዳ ጥሎ የመጣውን ጦር ሲያነጋግር የአለቃቸውን አስከሬን ትተው መምጣታቸው አሳፋሪ ድርጊት መሆኑን ጠቅሶ ተናግሮ ነበር።

አባቴ ደገሐቡር ጦርነት ላይ እያለ እናቴ የመጀመሪያ ልጅ ስለወለደች፣ ከጦርነቱ በድል አድራጊነት ሲመለስ፣ አዲስ ልጅ እና ከአዜ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ የጦር ሜዳ ጀግና ሜዳሊያ ጠበቀው። ከኮሪያ ሲመለስ ባጠራቀመው ገንዘብ የመጀመሪያውን ኦስቲን የተባለች አንደ ቤቢ ፊያት የምታክል መኪና ገዝቶ ጓዳኞቹን ጭኖ ወደ አዲስ አበባ ለመዝናናት በየሳምንቱ መጨረሻ ብቅ ይል ነበር። ያን ጊዜ ጥላሁን ገሠሠ እየታወቀ የመጣበት ጊዜ ስለነበርና አባቴን ካፈራው የክብር ዘበኛ ሙዚቀኛ ክፍል፣ ከብዙነሽ በቀለ ጋር ይዘፍን ስለነበር "ጥላሁን ዛሬ እዚህ ይዘፍናል" ከተባለ አይቀርም ነበር።

ወደ ናዝሬትም አንዲሁ እየሄደ ይዝናና ነበር። እናቴ ከአባቷ ከአቶ አዳሙ ባይሳሴ ጋር ከሐረር መጥታ ናዝሬት ስትኖር ነበር የተዋወቁት። "የጋሼ ደምሴ ሚስት ቁንጅና ለጉድ ነው" እየተባለ አድአ በርጋ ድረስ ይወራ ነበር። በ1960 የመጀመሪያ ቤታቸውን በደብረ ዘይት ሠርተው ሲጨርሱ በመወለዴ አባቴ ደረጀ ብሎ ስም አወጣልኝ። ከኔ በፊት የተወለዱት አስክንድር፣ ዮናስ፣ እና ቅድስት ሲሆኑ ሐረር ከተዛወረ በኋላ ታናሽ እህቴ ሔዋን ተወለደች።

-11-

የጠሩ ውስጣዊ ችግሮችና የኩዴታው ፍንጮች

ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ፣ የኢትዮጵያ ጦር ውስጥ የነበሩት የበላይ መሪዎች በጥቅሉ በሁለት መደብ የሚከፈሉ ነበሩ። ደርግ ሥልጣን ሲይዝ ቀድሞ የነበሩትን መሪዎች በተለይ ከብርጋዲየር ጀነራል አስክ ሌተና ጀነራል ማእረግ የነበራቸውን በሙሉ አስሮ ነበር። ደርግ ስልጣን ከመያዙ በፊት ወደ 18 ሌተና ጀነራሎች፣ ወደ 29 ሜጀር ጀነራሎች፣ 98 ብርጋዲየር ጀነራሎች (አንድ የባሕር ሃይል ኣድሚራል ጨምሮ) ነበሩ። (የአናብስት ምድር ታደሰ ቱሌ ሳልሻኖ 107-111)

ከእነዚህ ውስጥ 11 ሌተናል ጀነራሎች፣ አራት ሜጀር ጀነራሎች፣ (አንድ ሪር አድሚራልን ጨምሮ)፣ እና 3 ብርጋዲየር ጀነራሎች፣ ከአምስት ኮለኔል መኮንኖች ጋር አለ ፍርድ ተገደሉ። የተቀሩት ብዙዎቹ ከሁለት እስከ ስምንት አመት በሕግ ፊት ሳይከሰሱ ፍርድ ቤትም ሳይቀርቡ በእስር ቆይተዋል። በዚህ ምክንያት ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ውስጥ በቂ ልምድ ያላቸውና ጠሩን ለመምራት ብቁ የሆኑ መኮንኖች በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ። የተፈጠረውንም አዛኝ አጥረት ለሚሚላት ብቁ ለሆኑ የበታች መኮንኖች ጊዜያቸውን ሳይጠብቁ ከፍተኛና አፋጣኝ እድገት

እያገኙ አለቦታቸው ተቀምጠው ከየቦታ ተመልምሎና የአጭር ጊዜ ሥልጠና ተሰጥቶት የሚመጣውን ጠር መለማመጃ አደረጉት።

በነዚህ በፖለቲካ አመለካከታቸውና ለደርግ ባላቸው ፍፁም የሆነ እምነት ስልጣን የተሰጣቸው፣ የበታች መኰንኖች እና ጊዜአቸውን ጠብቀው ባካበቱት ልምድና ትምህርት መሠረት ከፍተኛ ሥልጣን በያዙ መኮንኖች መካከል ከፍተኛ እለመግባባት ነበር።

የኔን አባት እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል። የሱ ዓይነት ደግሞ ብዙ ነበሩ። ደርግ ሥልጣን ሲይዝ በሌ/ኮረኔል ማዕረግ የሐረር ጦር አካዳሚ የትምሕርት ዲሬክተር ነበር። እዚያ ማእረግ ላይ ለመድረስ ወደ ሃያ አመት ፈጅቶበታል። ታዲያ የደቡብ አዝ አዛዥ ሆኖ ወደ ሲዳሞ ክ/ሐገር ሲሄድ የእዙ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊ ሆኖ የተመደበው እና የእዙ ሁለተኛ ባለስልጣን የኔ አባት ሌተና ኮነሬል እያለ እሱ በአስር አለቃ ማእረግ (የባለ ሌላ ማእረግ ተብሎ የሚታወቅና ከተራ ወታደር ቀጥሎ ያለ ማእረግ) የሙዚቃ ክፍል ጡሩንባ ነፊ የነበረ፣ የደርግ አባል የሆነ ወታደር ነበር። አሰር አለቃ ግርማ አየለ፣ አፋጣኝ እድገት ተሰጥቶት፣ የመቶ አለቃ ማእረግ ካገኘ በኋላ፣ ብዙም ሳይቆይ ሻምበል፣ ከዚያም ሻለቃ፣ ሌተና ኮነሬል፣ ሙሉ ኮነሬል መጨረሻም ብርጋዲየር ጀነራል ተብሎ፣ እድገቱ በኢህአዴግ አስኪያዝ ድረስ ቀጥሎ ነበር። በትክክለኛው ደንብ አንድ መኰንን ከአጨ መኮንነት ተመርቆ እስከ ብርጋዲየር ጀነራልነት ደረጃ ለመድረስ ከ24 እስከ ሰላሳ ዓመት ይፈጅበታል። ብዙዎቹ እንደውም ከሙሉ

ኮነሬል በላይ አያልፉም። ግርማ አየለ ግን ከ15 ዓመት እድገቱ ጋር የሚያስፈልገውንም ትምሕርት ሳይወስድ ብርጋዲየር ጀነራልነት ደርሶ ነበር።

በዚህ ዓይነት እድገት ያገኙ የጦር መሪዎች፣ ማንኛውንም ውሳኔ ከፖለቲካ ጋር ነበር የሚያገናኙት። ዓላማቸውም ከአገር በፊት የፓርቲና ያላቅማቸው የሚያሳድጋቸውን መንግሥት ደህንነት መጠበቅ ነበር። ለአገራቸው ብዙ ዓመት የደከሙ መኮንኖችን ተራ ምክንያት እየፈለጉ ፀረ አብዬተኛ ነው እያሉ በመወንጀል ሲያሳስሩና ሲያስገድሉ በአገር ላይ የሚያደርሱት ጉዳት አይታያቸውም። ለፓርቲያቸው ከጠቀመ ለአገርም ይጠቅማል ብለው ደምድመዋል።

በሌላ በኩል እድሜ ልካቸውን ስለ ወታደራዊ ሳይንስ እንጂ ስለ ፖለቲካ ግድ ሳይሰጣቸው፣ ከድሮ ጀምሮ በተለያየ ቦታና ኃላፊነት ላይ ተቀምጠው ይሰሩ የነበሩ ሙያተኛ መኮንኖች፣ ደርግ ከመጣ በኋላ ራሳቸውን ከፍተኛ አመራር ቦታ ላይ ቢያገኙም በድሮ ባሕሪያቸው ያካበቱትን ልምድ እንዲሁም ለሚያዙት ጦር ያላቸውን ፍቅር፣ አብሮት ባመጣው አዲስ ዘይቤ መቀየር አልቻሉም። በሥራቸው ያሉ ታታሪና ብቁ መኮንኖች ትናንት ከሙዚቀኛ ክፍል በመጣ የበታች ወታደር ሲታዘዙ ሲያዩ. እንደ ትክክለኛ የሚሊተሪ አሰተዳደር ሊቀበሉት አልቻሉም።

ይህ ሁኔታ በጦሩ ውስጥ በጣም የሰፋና አስከመጨረሻው ድረስ ቀጥሎ ብዙ ውድቀት ያስከተለ ነበር። ሌላ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል

በትግራይ ውስጥ የነበረው የሶስተኛ ሠራዊት ጦር አዛዥ ሚ/ጀ/ሙላቱ ነጋሽ ሆነው ሳለ ከበላያቸው ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ የተመደበው ሃምሳ አለቃ ለገሰ አስፋው ነበረ። ጀ/ሙላቱ ከክብር ዘበኛ መኰንኖች ማሰልጠኛ የተመረቁና በሐረር ጦር አካዳሚ አስተማሪ የነበሩ በጠሩ ውስጥም በተለያዩ ቦታዎች በመሪነት የሰሩ ጀኔራል ነበሩ።

ለገሠ አስፋው ደግሞ የደርግ አባል ሆኖ ወደ ሲቪል ሥራ አስከገባ ጊዜ ድረስ በሃምሳ አለቃ ማአረግ የመገናኛ ክፍል ውስጥ ሲሰራ የነበረ አንኳን ጦር መርቶ ሊያውቅ ቀርቶ ስለ አመራር ውይይት ሲደረግ አንኳን በአካባቢው ዝር ማለት የማይፈቀድለት ወታደር ነበር።

-12-

ደርግ ሲቋቋም ወታደሮች የበላይ አለቆቻቸውን ማሰር ጀምረው ነበር። እኔ ያን ጊዜ አድሜዬ ገና ከአምስት ወደ ሰድስት አመት ገደማ ቢሆንም አንዳንድ ነገሮች ትናንት እንደሆኑ ያህል ቁልጭ ብለው የሚታወሱኝ ነበሩ።

ትዝ ከሚሉኝ አንዱ ወታደሮች አለቆቻቸውን አያሰሩ ነው አና እኛም ቤት ሊመጡ ይችላሉ እየተባለ የሚወራበት ጊዜ ነው። በዛን ሰሞን፣ የናቴ አባት፣ እያቴ አባባ አዳሙ፣ ሁልጊዜም ሊጠይቁን ሲመጡ እንደሚያደርጉት ረጅም ሌም ዋን ጠመንጃ አንግተው ፤ ረጅም 45 ካሊበር ሽጉጥ ከጉን ሸጠው፤ ዝግ ባለ አርምጃ ወደ ቤታችን ሲያመሩ፣ አሁን ድረስ ጭንቅላቴ ውስጥ ተቀርጾ ይታየኛል። አያቴ የታወቁ አዳኝ የነበሩና በቱሪዝም ሚኒስቴር በኩል የሚመጡ የውጭ አንግዶችን አደን አየያዙ የሚሄዱ፣ ስለተለያዩ አውሬዎችና አደን ከፍተኛ አውቀት የነበራቸው የወንዶች ወንድ ነበሩ። አዳሙ ባይሳሌ ይባላሉ። ከማርሻል ቲቶ ጋር ሳይቀር አደን ሄደዋል። አርሳቸው እንደ ሚሉት ከሆነ አንጣጥረው ከሩቅ አሱ ባልጠበቀው ሁኔታ አንድ አጋዘን ግንባሯን ብለው ሲጥሉ በመደነቅና በመደሰት የያዘውን ጠመንጃ ሸልሟቸዋል። ታዲያ በዚያን ጊዜ አንድ ቀን

አባባ አዳሙ የያዙትን መሣሪያ ከትከሻቸው ላይ እያወረዱ "አስቴሪ እንደምን ሰንብተሻል? ያ ቢጋሻው ጅጅጋ ብረት ረክሷል ብሎ ልኩብ አዚያው ልወርድ መጣሁ" ብለው እናቴን ሲሰሙ ትዝ ይለኛል። ያን ሁለ መሣሪያ ይዘው ተጨማሪ ለመግዛት ወደ ጅጅጋ ለመሄድ ብዙ መንገደ መምጣታቸው አሰከዛሬ ይገርመኛል።

አባባ አዳሙ በመጡ ሁለተኛው ቀን በነበርንበት የሐረር አካዳሚ መኰንኖች መኖሪያ ካምፕ ውስጥ ብዙ ግርግር ይታይ ጀመር። አያቴ "እንድ ሰው አስቲ አዚህ ቤት ዝር ይበል ቅንድቡን ብዬ ነው የምጥለው።" አያሉ ሲቁነጠነጡ አባቴ ደግሞ መሣሪያውን ሲፈትሽ ትዝ ይለኛል። ከሐረር አካዳሚ የደርግ አባልነት ሰው መርጣችሁ ላኩ ሲባል የሚላከውን ሰው የመረጡት የኔ አባትና የአካዳሚው አዛዥ ነበሩ። በጊዜው የነበሩት አዛዥ ጀ/ተፈሪ ባንቲ ነበሩ። በቅርቡ ጀ/ግዛው በላይነህን ተክተው የመጡ ስለነበር ካሉት የበታች መኰንኖች ቢሄድ ብዙም የማያጉድል ተብሎ የተመረጠው ሻምበል ብርሃኑ ባይህ ነበር። ከብዙ ዓመት በኋላ በሚሊተሪ ሳይንስ አውቀታቸው ከታወቁት መኰንኖች አንዱ ጀ/ተሰፋዬ ትርፌ ሐረር የመኮንኖች ክበብ ከአባቴ ጋር ቆሞ ሲያወራ

"ጀነራል ያንጊዜ አኮ እኔን ሊልኩኝ ይችሉ ነበር" ሲል እኔም የጠረጴዛ ቴኒስ ጨዋታዬን ጨርሼ ኪኖቶዬን እየተጐነጨሁ ቆሜ አዳምጥ ነበር።

"ያኔ ማን አዚህ ይደርሳሉ ብሎ ጠብቆ! የአንተ ሰም ተነስቶ ነበር። ለት/ቤቱ ታሰፈልጋለህ ብለን ወሰንን" አለ አባቴ ፈገግ እያለ። ብ/ጀነራል ተሰፋዬ ትርፌ በዚያን ጊዜ በኮነሬል ማእረግ የሐረር ጦር አካዳሚ አዛዥ

ነበረ። ከአባቴ ጋር በአሜ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የሐረር ጦር አካዳሚ አሰተማሪ ነበር። (ከድሮ ጀምሮ አንተ ነበር የምለው)

"ለነገሩ ያን ጊዜ ጃንሆይን ከሥልጣን አውርደው አዲስ መንግሥት ይመሠርታሉ ብሎ ያሰበ አልነበረም። እንዳውም ጃንሆይ ይጠቀሙባቸዋል ተብሎ ነበር የሚነገረው! አገር እንዲመሩ ተብሎ ቢመረጡማ እነዚያን ማን ይልክ ነበር።" አባቴ ይህን ሲል ድምጹን ዝቅ ለማድረግ አለመሞከሩ አስገርሞኝ ነበር።

የዚህን ዓይነቱን ውይይት በግልፅ የሚያካሄዱት ቀድሞ የጃንሆይ የሐረር ቤተመንግሥት በነበረውና በኋላም የአንደኛው ጦር የመኰንኖች ክበብ በሆነው ግቢ ውስጥ በረንዳ ላይ ከነበረው የጠረጴዛ የቴኒስ ፊት ለፊት ቆመው ነበር።

በጦሩ አመራር ውስጥ ለህዝብ ግልፅ ያልነበረ፣ በደርግ አባላትና በደጋፊዎቻቸው እንዲሁም በትምህርትና በልምድ ጊዜያቸውን ጠብቀው ከፍተኛ ስልጣን ላይ በደረሱ የበላይ መኰንኖች መካከል ከፍተኛ ቅራኔ ነበር። አባቴ 1966 ለውጥ ሲመጣ ከዳር ሆነው ይመለከቱ ከነበሩት የበላይ መኮንኖች ውስጥ አንዱ ነበር። የደርግ አባሎች ጀነራል መኮንኖችን ካሰሩ በኋላ የቀሩት የበላይ መኮንኖች አንደ አባቴ ሌተና ኮነሬል እና አንዳንድ ሙሉ ኮነሬሎች ብቻ ነበሩ። አባቴ የዘመቻና የዕዝ አዛዥ እየሆነ ነበር የሰራው። በ1969 ሙሉ ኮነሬል፣ 1972 ብርጋዲየር ጀነራል ከዚያም በ1977 ሜጀር ጀነራልነት ሲሾም፣ የደረሰበት የሹመት

አድገት የደርግ መንግሥት ባይመጣም ሊደርስበት ወይም ሊያልፈው የሚችል ደረጃ ነበር። የደረሰበትም የሥልጣን ደረጃ፣ በራሱ ጥረት እና በሥራው ውጤት አንጂ ለመንግሥት ባለው ታማኝነት አልነበረም። አንደአባቴ ጊዜያቸውን ጠብቀው በሥራቸው ውጤት ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ ጀነራሎች ለውጡ ሲመጣ ተራ ወታደር፣ አስር አለቃ፣ ሃምሳ አለቃ፣ ም/መቶ አለቃ፣ የነበሩ እነሱ ከ38 ዓመት አገልግሎት በኋላ የደረሱበት ደረጃ ላይ በ15 ዓመት ከደረሱ ጀነራሎች ጋር አብረው ይሰሩ ነበር።

ለውጡ ሲመጣ ምንም አንኳን የራሱ መሬት አንዲሁም ብዙ የወላጆቼ ንብረት የተወረሰ ቢሆንም ለውጡን አልተቃወመውም። አንዳንድ ውሳኔዎችን በሙሉ ልብ ደግፎ ሲናገር አንዳንዶቹን ደግሞ አጥብቆ ይወቅሰ ነበር። መሬት ላራሹ፣ የመሠረተ ትምሕርት፣ የብሔረሰቦችን እኩልነት፣ የሰውን እኩልነት በተመለከተ የተወሰደውን እርምጃ ብዙ ጊዜ አንደምሳሌ እየጠቀሰ ለውጡን ደግፎ ይከራከር ነበር። በተለይ ከቀድሞ ወዳጆቹ ጋር በኢትዮጵያ የአንድ ሰው አምባገነን መንግሥት እየሰፈነ መምጣቱንና ወደ ሲቪል መንግሥት የተደረገው ሽግግር የውሸት ሽግግር መሆኑን፣ የራሱንም የሸንጐ ምርጫ ጨምሮ፣ የምርጫው ሂደት የህፃን ጨዋታ ዓይነት መሆኑን ደጋግሞ ይናገር ነበር። የነበረውን አመለካከት ብዙ ጊዜ በግልፅ ይናገር ነበር። አንዳንዴ የዚህ ዓይነት ሃሳቡን ያካፍላቸዋል ብዬ ከማልጠብቀው ሰዎች ጋር በግልጽ ሲወያይ አሰማ ነበር።

አንድ ቀን ጀ/ወርቁ ቸርነት ቃኘው ጦር ሠፈር የሚገኘው የአባቴ መኖሪያ ቤት ለአራት መጥተው ሲወያዩ አመሹ። አባቴ ከጀ/ወርቁ ቸርነት ጋር ሐረር እሱ የጠሩ አዛዥ አሳቸው የፖለቲካ መምሪያ ሐላፊ ሆነው ብዙ ዓመት ሰርቷል። ጀ/ወርቁ ከሌ/ኮ/መንግሥቱ ጋር አብሮ አደግ የነበሩ መሆናቸውን ሌ/ኮ/መንግሥቱ በስጡት ቃለ ምልልስ ላይ "ከአብሮ አደግ ጓደኞቼ አንዱ ጀነራል ወርቁ ቸርነት ነበር። አብረን ነው ያደግነው።" ብለው ስለቅርበታቸው ብዙ ካወሩ በኋላ፣ አሰመራ ለምን ከአባቴ ጋር አንደተመደቡ አንዲህ ብለው ገልጸዋል።

"ወርቁን እዚያ አንዲሄድ ያደረግሁበት ምክንያት ታማኝና ሃገሩን በቅንነት ያገለግላል ከሚለው እምነቴ በተጨማሪ ከጀነራል ደምሴ ቡልቶ ጋር ስለሚግባባ ነበር። በዚያ ሰዓት በደምሴ ቡልቶ ላይ ጥርጣሬ የሚያሳድሩ አንዳንድ ነገሮች ነበሩ። እሱ አንግዲህ ደምሴ ቡልቶ ጉበዝና ችሎታ ያለው ጥሩ መኮንን ሆኖ ነገር ግን ትንሽ የማፈንገጥ ነገር ስለሚታይበት በነወርቁ ያጠርኩት ለዚህ ነበር።" (ሌ/ኮ መንግሥቱ ትዝታዎች ገጽ 319)

ጀነራል ወርቁ ቸርነት ከአባቴ ጋር ቁጭ ብለው ሲወያዩ ላዳመጠ ሰው ግን ለአገራቸው የነበራቸው ፍቅር ለመንግሥቱ ታ/ማርያም በነበራቸው ቅርበት የተወሰነ አንዳልነበረ ግልፅ ነው።

አባቴ "ወርቁ ይህ ሁኔታ አስከመቼ ነው በዚህ መልክ የሚቀጥለው? መሠረታዊ ለውጥ ካልተደረገ ይች አገር ከፍተኛ አደጋ ላይ ነው

የምትወድቀው" ብሎ ሲጀምር ፣ ጀ/ወርቁ ወዲያው ተቀብለው "ጀነራል እኛ እኮ ለህዝብ የተሻለ ሥርዓት እናመጣለን ብለን እንጂ፣ የአንድ ሰው አምባገነን መንግሥት ለመመሰረት አልነበረም ለውጡን የደገፍነው" አሉ።

የፖለቲካ ኃላፊ እንደዚህ ሲናገር ሰምቼ ስለማላውቅ ግራ ገባኝ። ይህ ሰው ተናግሮ ለማናገር ፈልጉ ቢሆንስ? አባቴ ግን ከዚህ በፊት ሁሉ እንደዚህ በነፃ በየቀኑ ሲወያዩ እንደኖሩ ዓይነት ቀልዶችን ሁሉ በመሐል እየጣለ ውይይቱን ቀጠለ።

አባቴ በጠሩ ውስጥ ስለነበሩት የተለያዩ ችግሮች በተደጋጋሚ እየተበሳጨ ይናገር ነበር። ብዙ ችግሮች ከድርጅታዊ እና ካወቃቀር ችግር የመነጩ ነበሩ። በተለያየ ጊዜ መንግሥት በተለይ ጠሩን በተመለከተ የሚወስዳቸውን ውሳኔዎች ይተች ነበር። የጠሩ አወቃቀር ወታደራዊ ዲሲፕሊንን እንዳፈረሰና ፖለቲካ እና የሚሊተሪ ሳይንስ ብዙ ጊዜ ሲጋጩ ለፖለቲካ ቅድሚያ መሰጠቱ ያበሳጨው ነበር።

ችግሩ መፍትሄ እንዲፈለግለት በበኩሉ ያለውን ሃሳብ ከማቅረብም በላይ፣ በጊዜው የታወቀው የኩባ ጀነራል የኢትዮጵያን ወታደራዊ አቋም ለመገምገም በመጣ ጊዜ የተለያዩ የጠር ክፍሎችን አዙሮ ካስጐበኘው በኋላ፣ በጠሩ ውስጥ ለነበሩት ችግሮች፣ መፍትሄ መፈለግ አማራጭ የሌለው መሆኑን ገልጾ አሳምኖት ነበር። ጀኔራል ኦቾዋ ኦንጐላ የነበረው የኩባ ጠር አዛዥ የነበረና በሱማሌም ጠርነት ጊዜ ኢትዮጵያ የነበረው የኩባ ጠር

የበላይ አዛዥ ነበር። ጀ/ኦቾዋ በኩባ ጠር ውስጥ አሉ ከሚባሉት ጀነራሎች በመጀመሪያ ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ነበር። ጀነራል ኦቾዋ ለሉ/ኮ/መንግሥቱ በሰጠው ሪፖርት ላይም የገለጸው በጠሩ ውስጥ መደረግ የሚገባቸውን የሥርዓትና የድርጅት ለውጦች ነበር። ሪፖርቱን ከስፓኒሽ ወደ አማርኛ የተረጐሙት የሌ/ኮ መንግሥቱ ዋና አስተርጓሚ አቶ ግርማ በሻህ ስለዚህ ሪፖርት ሲገልጹ፣ እንደዚህ ብለዋል፣ "ኦቾዋ የጎሬዘዳንቱ ወዳጅ ነበሩ። የኢትዮጵያ ሁኔታ በጣም ያሳስባቸው ስለነበር አንድ ቀን ከአንጎላ ከተፍ ይላሉ። የትም ሳይሄዱ ቀጥታ ከቦሌ ወደ ጎሬዘዳንቱ ቢሮ ይመጣሉ። ሁለቱ ወዳጆች ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ኦቾዋ "ኤርትራ ውስጥ ያለው ሁኔታ ደስ ስለማይል በዚያ ተገኝቼ ሁኔታውን ለማጣራት ነገ ጠዋት ወደዚያ ማቅናቴ ነው ስመለስ በሰፊው እንወያያለን" ብለው ወጡ።

"በወቅቱ በኤርትራ የነበረውን ሠራዊት ያዝዙ የነበሩት ጀኔራል ደምሴ ቡልቶ ነበሩ። ኦቾዋና ደምሴ በሶማሌ ጠርነት ጊዜ አብረው የተዋጉ ጓዳኛሞች ነበሩ። ኦቾዋ በደምሴ ቡልቶ ባልደረባነት ለአምስት ሳምንት ኤርትራንና ትግራይን ጉብኝተው ከተመለሱ በኋላ፣ እዚህ አዲስ አበባ ለጥቂት ሳምንታት ሀቡዕ ገብተው የጻፉትን ባለ አምስት ጥራዝ ሪፖርት ለጎሬዘዳንቱ አቀረቡ። ያን ሪፖርት ከስፓኒሽ ወደ አማርኛ የተረጎምሁት እኔ ነኝ። ያ ሪፖርት በብዙ መልኩ ታሪካዊ ነው። በኤርትራና በትግራይ የነበረው ወታደራዊ ሁኔታ ትክክለኛ ገጽታ ምን እንደሚመስል ከማሳየቱ ባሻገር ሠራዊቱ የመከላከሉን ተግባር በምን ዓይነት ዘዴ ማካሄድም እንዳለበት ምክር የሚለግስ ጽሁፍ ነው። ጽሁፉ የእነ ጀኔራል ደምሴ ቡልቶንም ራዕይ

የሚያንጸባርቅ መሆኑ ግልጽ ነው። ግን ምንም እርምጃ አልተወሰደም።"
(ኢትዮጵ ቅጽ 5 ቁጥር 048/95 ገጽ 34 ሰኔ 1995 ዓም ከአቶ ግርማ በሻህ የከ/ል መንግሥቱ አሰተርጓሚ የነበሩ፣ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ)

ጀ/ኦቾዋ ኩባ ተመልሶ ስሙ በጣም እየገነነ ከመጣ በኋላ ካስትሮ የወንጀል ክስ መስርቶበት፣ የሞት ፍርድ አስፈረደበት። በየአህጉሩ እየሠፈ በተዋጋለት አገርና መንግሥት በጥይት ሕይወቱ አልፋለች።

-13-

ብዙ ጊዜ አባቴን ለመጠየቅ የሚመጡ እንግዶች ነበሩ። ብዙዎቹ ኮሎኔሎችና ጀነራሎች ነበሩ። አልፎ አልፎ የሲቪል ባለስልጣናት ይመጣሉ። አባቴ ብዙ የሚያቀርባቸው ሰዎች ቢኖሩም የልብ ጓደኛ ብዙ አልነበረውም። የቅርብ ጓደኛ ብሎ የሚጠራቸው በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ። ከነዚህም አንዱ ጀ/መርዕድ ንጉሤ ነበር። የክብር ዘበኛ ካዴት ኮርስ ለመካፈል ከተመዘገቡበት ጊዜ ጀምሮ ነበር ጓደኝነታቸው። ሲገናኙ ስለ ጠሩ ሁኔታ፣ የት ምን መደረግ እንዳለበት፣ ማን ምን እየሰራ እንደሆነ፣ ማን የት እንደተዛወረ፣ ለምን እንደተዛወረና በጠሩ ውስጥ ስለነበሩት የተለያዩ ችግሮች በቀር ስለሌላ ጉዳይ አያወሩም። አልፎ አልፎ ስለ አንዳንድ የሲቪል ወይም የደርግ ባለስልጣኖች አንስተው እንኳ ቢወያዩ ብዙ ጊዜ ከጠሩ ጋር በተገናኘ ጉዳይ ላይ ነበር። ታዲያ በማንኛውም ውይይት ላይ እኛ ልጆች ተቀምጠን ማዳመጥ ይፈቀድልን ነበር። በጠሩ ውስጥ ስለሚከናወነው ማንኛውም ጉዳይ ከትምህርታችን በላይ ነበር የምናጠናው። አልፎ አልፎ ጣልቃ ሁሉ እየገባን ስንጠይቅ አባቴ ጊዜውን ወስዶ ያስረዳን ነበር። በተለይ ታላቅ ወንድሜ የአንደኛ ዙር ብሔራዊ ውትድርና ዘምቶ

ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ ሲመለስ እንደልቡ መጠየቅና ሐሳብ መስጠት ሁሉ ጀምሮ ስለነበር ተሳትፎአችን እየጠነከረ መጥቶ ነበር።

ይህን ዓይነት ተሳትፎ ግን ጀ/ፋንታ በላይ ብቅ በሚሉበት ጊዜ አይፈቀድልንም ነበር። ጀ/ፋንታ እና አባቴ ከባሬንቱ ጦርነት በፊት ብዙም አይቀራረቡም ነበር። እንዲሁ በተለያዩ ሰብሰባዎች ላይ ከመገናኘት በቀር በቅርብ አንድ ላይ ሠርተው አያውቁም ነበር። ሻዕቢያ ባሬንቱ የነበረውን የኢትዮጵያ ጦር ደምስሶ ከተማውን ከተቆጣጠረ በኋላ ብዙ መሣሪያ፣ ጥይትና ቀለብ በቦታው አከማችቶ በደንብ መሽጉ ለተከታይ የማጥቃት እርምጃ የተዘጋጀበት ጊዜ ነበር።

ጀ/ደምሴ ያን ጊዜ ሐረርጌ የነበረው የእንደኛው አብዮታዊ ጦር አዛዥ ነበር። የመከላከያ ሚ/ር ባሬንቱን ለማስለቀቅ ከፍተኛ ጥረት ለማድረግ ሲወሰን ከሐረር የተወሰነ ጦር ወደ ኤርትራ አዛውሮ በተለያዩ የጦር ሐይሎች የተቀነባበረ የማጥቃት እርምጃ ለመውሰድ ዝግጅት ተጀመረ። ጀ/ደምሴ የጦር ኃይሎች ኮሚቴ የዘመቻ ዋና አስተባባሪ ሆኖ ባሬንቱን ለማስለቀቅ ኘላን ካወጡት አዛዦች አንዱ ነበር። ጀ/ፋንታ በላይም አብረውት ከሰሩት ጀነራሎች አንዱ ነበሩ። (በዚህ ዘመቻ ግዜ ጀ/ደምሴ የመዘገበው ሙሉ የጦር ሜዳ ማስታወሻ በመጨረሻው ላይ ቀርቧል)

"ፋንታ...እኔ አኮ ደምሴ እንደዚህ እንደሆነ መች አውቅ ነበር።" ብሎ አለኝ ሲል ጋሽ መርዕድ ትዝ ይለኛል። ከዚያን ጊዜ በኋላ አባቴ አዲስ

አበባ ለስራ ሲመጣ ጀ/ፋንታ ማምሻቸውን ብቅ ይሉና የሳሎን በር ተዘግቶ ለብቻቸው ይነጋገሩ ነበር። የእኛ ቤት ሳሎን በር እንግዳ ውስጥ ሆኖ ተዘግቶ ስለማያውቅ፣ የሚጠጣ አቅርበን መውጣት የተለመደ አልነበረም። ስለዚህ የሚነጋገሩት ምስጢር ከበድ ያለ መሆኑን ለመገመት አልተቸገርንም።

ከጀ/ፋንታ ጋር የግል ውይይት በሚካሄድበት ሰሞን አንድ ቀን አባቴ እኔንና ታላቅ ወንድሜን ዮናስን ጠርቶ "ዎክ አናድርግ" ብሎን ከቦሌ መንገድ ከሚገኘው ቤታችን ተነስተን ወደ ቦሌ አውሮኘላን ማረፊያ በዝግታ መጓዝ ጀመርን።

አባቴ ረጋ ብሎ አካባቢውን እየቃኘ "ይች ህይወት ታጓጓለች። የምትወደውን ስውና ይህን የሚያምር ተፈጥሮ ጥሎ ለመሄድ መወሰን ቀላል አይደለም።" አለን። አሁንም ፈገግ ብሎ "ፈሪ ማለት ይችን ዓለም ለቀመለት ዓላማ ጥሎ ለመሄድ ያልወሰነ ማለት ነው። ሌላ ነገር የለውም።"
አባታችን መልስ እንድንሰጠው ዓይነት አልነበረም የሚያነጋግረን። ወደ አየር ማረፊያው መግቢያ አካባቢ ስንደርስ መንገዱን ተሻግረን ወደመጣንበት አቅጣጫ መመለስ ጀመርን። አሁንም ዝግ ብለን ነው የምንራመደው።

"እዚህ የሰበሰበው ቅልብ ጦር አለ... ጦርነት አይቶ አያውቅም... ሁኔታዎች ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ ነው... በዚህ ሁኔታ መቀጠል

አንችልም። መደረግ ያለበትን አስፈላጊ ለውጥ ለማምጣት የምንችለ
ይህን ሰውዬ በማንሳት ብቻ ነው።"
ስለነበሩት ችግሮች ሲያጫውተን የመጀመሪያው አልነበረም፤ ስለመንግሥ
ግልበጣ ግን እንደዚህ በግልፅ ሰምተን አናውቅም። ዝም ብለን እያዳመጥ
የሰማነውን እያወጣን እያወረድን እኔና ወንድሜ ከአባታችን ጋ
መንገዳችንን በዝግታ ቀጠልን።

-14-

የሌ/ኮ መንግሥቱን አምባገነን የደርግ መንግሥት ለመጣል የተደረገው ሙከራ

ግንቦት 8 ወደ ከሰዓት በኋላ ቦሌ መንገድ ከነበረውና የምሰራበት መ/ቤት ውስጥ አያለሁ በዝቅታ የሚበር የተዋጊ አውሮፕላን ድምፅ የመ/ቤቱን ግንብ፣ ነቅንቀት አለፈ። በአሰደንጋጩ ድምፅ የተረበሸ ሠራተኛ ከየቢሮው እየወጠ ወጣ። እኔም ተከትዬ ወጣሁ። ትንሽ ቆይቶ ተዋጊ ሄሊኮፕተሮች እየበረሩ ወደ አብዮት አደባባይ አቅጣጫ አለፉ። ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ያየዋኋቸው ስለነበር የማንንጥ እንዳልነበሩ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም። ሠራተኛው ተደናግጠ ሁሉም አቃውን እየሰበሰበ ከቢሮው በፍጥነት እየለቀቀ ወደየቤቱ ሲሄድ እኔም ወደቤቴ አመራሁ።
አቤት ሰደርሰ የአህቴ ባለቤት ግርማ ከበደ ከአንድ ጓደኛው ጋር ሽጉጥ ታጥቆ በረንዳው ላይ ወዲያ ወዲህ ሲል ደረስኩ። "መክላከያ ግርግር አለ" አለኝ።
ወደ ውስጥ ገብቼ ወደ በረንዳው እንደተመለስኩ፣ ወታደሮች የጫኑ ከባድ መኪኖች በቦሌ መንገድ ሲያልፉ ተመለከትኩ። "አይ ይሄ ነገር ዓላማረኝም"

"ምን ይመስልሃል?"

"መፈንቅለ መንግሥት እየተደረገ ይመስላል"

በዚህ መሃል ብዙ ወታደሮችን የጫነ ከባድ መኪና ወደቤታችን ወደሚወስደው መንገድ ታጥፎ በራችን ላይ ሲደርስ ቆመ።

"ጉድ ፈላ!" ብለን ተያየን።

በሩ ተንኳኳ። ግርማና ጓደኛው አዩኝ። ጓደኛው ወደኔ እየተመለከተ "ክፈትላቸው!" አለኝ። ባልከፍትም አዚህ ድረስ ከመጡ መግባታቸው አይቀርምና ወደ በሩ አመራሁ፤ ስከፍት ምን እንደሚደርሰብኝ እያሰብኩ።

በሩን ስከፍት የማውቀውን ሰው መልክ አየሁ። ደስታ እና ግራ መጋባት አንድ ላይ ተሰማኝ። የአባቴ አጃቢ አሰር አለቃ ጌታቸው ከነሙሉ ትጥቁ ቆሟል። ከኋላው ሌላው የአባቴ አጃቢና ሁለት ከዚህ በፊት ያላየኋቸው ወታደሮች አሉ። ከባድ መኪናው እነሱን ካወረደ በኋላ፣ ወደመጣበት ተጠምዝዞ ወደቦሌ መንገድ ሲገባ በራፉ ላይ ከቆሙት ወታደሮች ጋር ሰላምታ እየተለዋወጥን ወደ ውስጥ ገባን። ግርማና ጓደኛው ከወታደሮቹ ጋር ስጨባበጥ ሲያዩኝ ትንሽ ተንፈስ አሉ።

ወታደሮቹን ወደ አዲስ አበባ ይዘው የመጡት ጀነራል ቁምላቸው ደጀኔ ነበሩ።

ከቢሮዬ ወጥቼ ዋናው መንገድ ላይ ወደቆመው ጥቁር ሊንከን ታውን ካር (ሌመዚን ተብሎ የሚጠራው) ተጠጋሁ። ወዲያው ከወንድሞቼ ለይቼ የማላየው አብሮ አደግ ጓደኛዬ ነአምን ዘለቀ በሩን ከፍቶ ወረደ። ለእሱ በፍጥነት ሰላምታ ሰጥቼ ፊቴን ከኋላ ወደ ተቀመጡት አንግዳ አዞርኩ። እኚህን ሰው በአካል ካየኋቸው ከ13 ዓመት በላይ ሆኖኛል። መኪናው የቀመው በኪምብሪጅ ማሳቹሰት በማሳቹሰት አቨኑ ላይ ከሚገኘው ቢሮዬ ፊት ለፊት ነው። ዘመኑም በፈረንጆች አቆጣጠር 2002 መጨረሻ ወር ላይ ነበር። በኤርትራ በረሃ ከተያየን ወዲህ በስልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘኋቸው ባለፉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ነው። ሰውነታቸው ተቀይሯል። በጠና ታመው ለሕክምና ነበር የመጡት። ወደ በሩ ጠጋ ብለው ሰላምታ ተለዋውጠን ተሳሳምን። ከለበሱት ጥቁር ካፖርት ስር ሙሉ ሱፍ ለብሰዋል። ሉጫ ፀጉራቸውን ወደ ኋላ መሸሹን በማያሳውቅ ሁኔታ ወደፊት ልምጭስ አድርገው አበጥረውታል። ከፊታቸው መጥቀር በስተቀር መልካቸው እንዳለ ነው።

"እንኳን ደህና መጡ ጀነራል!" ፈገግ ብዬ ጨበጥኳቸው ።

"እንኳን ደህና ቆየኸኝ!" አሉ ጀነራል ቁምላቸው ደጀኔ እንደምንም ፈገግ ብለው። ከቦስተን ኧውሮፕላን ማረፊያ ነበር በቀጥታ የመጡት።

ብዙም ጊዜ ሳናጠፋ እኔም ወደ መኪናዬ ሄጀ እየተከታተልን ለሕክምና ወደሚገቡበት ሆስፒታል አመራን። ጀነራል ቁምላቸው በጠና ታመው ስለነበር እዚያው ሆስፒታል እንዲያድሩ በመደረጉ ከነአምን ጋር ስንጫወት አምሽተን ወደቤት አመራን።

ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ጀ/ቁምላቸው ሕክምና ሲደረግላቸው ከረሙ፣ በየቀኑ ጥቂት ሰዓታት አብረን እናሳልፍ ነበር። አልፎ አልፎም ስለተለያዩ ጉዳዮች እንጫወታለን። ብዙ ጊዜ ከአባቴ ጋር ስላሳለፉት ስለራሳቸውም ታሪክ ያወጉኝ ነበር። ጨዋታ ያውቃሉ። በሽታ ጠንቶባቸው አንዲህ ከተጫወቱ በጤናቸው ጊዜ ቢሆንማ እንዲት ያሳምሩት እንደነበር እየገመትኩ ባለፉት 13 ዓመታት በአካል ተገናኝተን አለመጫወታችን ያሳዝነኝ ነበር።

"ጀነራል በቴፕ ብቀዳዎት ምን ይመስልዎታል?" አልኳቸው አንድ ቀን ሆስፒታል አልጋ ላይ ጋደም ብለው ሲያጫውቱኝ ከቆዩ በኋላ።
"ይቻላል። ምን አለ የማውቀውን ሁሉ ልነግርህ ፈቃደኛ ነኝ" አሉኝ፤ ደከም ባለ ድምፅ። በሽታው ጠንቶባቸው ከጥቂት ደቂቃዎች በላይ ሳያቋርጡ መናገር አይችሉም ነበር።

አንዳንድ ጊዜም ሲደክማቸው አይና ጥያቄ ማቅረቤን አቆማለሁ። በፀጥታ አንተያያለን። አንዳንዴም ብዙ ጊዜ ስለማላገኝ ምሳዬን ይዤ አሄድና በዝምታ እየተያየን ምሳዬን በልቼ የቀኑን ጋዜጣ ሰጥቻቸው አሄዳለሁ። አንዳንድ ቀን ደግሞ በጣም ተሸሏቸው ቁጭ ብለው ጨዋታ ለማውጋት ተዘጋጅተው ይጠብቁኛል። በነዚያ ቀናቶች በጭንቅላቴ ሲብላሉ የቆዩትን የተለያዩ ጥያቄዎች አዥጐደጉዳለሁ። ያገኘኋቸው መልሶች አንዳንዱ አጥጋቢ አንዳንዱ ደግሞ የባሰ አደናጋሪ ነበሩ። ጥያቄ ጥያቄን እየወለደ ለብዙ ሰዓት እንወያይ ነበር። በቴፕም እየተቀዱ አጫውተውኛል።

"ጀነራል አንድ መጽሐፍ ጀምሬ ነበር፤ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል በ92 በፈረንጆች አቀጣጠር ነበር የጻፍኩት፤ ነገር ግን ልጨርሰው ባለመቻሌ እስከዛሬ ቀቀምጧል። ለመጨረስ ብዙ ጥያቄዎችን መመለስ አለብኝ። ለእነዚያ ደግሞ እስካሁን መልስ አላገኘሁላቸውም" አልኳቸው መልሱን ከሳቸው በለኮንድ ውስጥ ተቀብዬ ለመሄድ እንደተዘጋጀሁ ዓይነት በመቻኮል።
"ለለምንድነው የምትፅፍው?" አሉኝ መልሱን በመገመት ዓይነት።
"ስለ አባቴ እንዲሁም ኤርትራ ያንጊዜ የመጣሁ ጊዜ ስላየሁት፣ እንዲሁም ስለ ኩዴታው..."
"የምትፈልገውን ሁሉ ጠይቀኝ፤ የማውቀውን እነግርሃለሁ"
ሆስፒታል ከገቡ ቀን ጀምሮ ራስ ላይ የምትጠለቅ የሹራብ ቆብ አድርገው ነበር የሚውሉት፤ ለሙቀት ብለው ነው። ሲያነቡ የሚያደርጉትን መነፅራቸውን አጥልቀው በሕመም ላይ ቢሆኑም ፈገግ እያሉ ነበር የሚመለከቱኝ።

"እም ብዙ ሰዎች አነጋግሬአለሁ። ነገር ግን እውነቱን ለማግኘት አስቸጋሪ ነው። አንዳንዱ ያጋንናል። አንዳንዱ ደግሞ ደስ እንዲለኝ ያልተደረገ ወይ ያልተባለ ነገር ይጨምራል። ሌላው ደግሞ የሰማውን እንዳየ አድርጐ ያወራል። እኔ ማወቅ የምፈልገው፣ የምጠይቀው ሰው ያየውን፣ ያደረገውን፣ ወይም በቦታው ላይ በጆሮው ያዳመጠውን ነው። እና ያንን ብቻ ተናግሮ የሚያቆም ሰው ጥቂት ነው። ታሪኩ እንደነበር እንዲነገር ነው የምፈልገው። እርሶ በቦታው ነበሩ። ሁሉም ቦታ አልነበሩም፤ ነገር ግን ያደረጉትንና

ያዩትን በቦታው ላይ የሰሙትን ቢነግሩኝ በጣም ደስ ይለኛል። ለመፀሐፈ ይጠቅመኛል።"

"ምን አለ ታዲያ ስለሁሉም መወያየት አንችላለን"
በዚህ ሁኔታ ነበር ጀነራል ቁምላቸው ያደረጉትን ያዩትንና በቦታወ የሰሙትን ያጫወቱኝ።

∞∞

ጀ/ቁምላቸው ስለ መፈንቅለ መንግሥት የማካሄድ ዓላማና ጥንሰሳ ከጀነራል ደምሴ ጋር መወያየት ከጀመሩ ዓመታት አልፈዋል። ዓላማውን አምነውበት የተቀበሉትም መጀመሪያ ከጀነራል ደምሴ ጋር ከተነጋገሩበት ቀን ጀምሮ ነበር። ያኔ የሚጓዙበት ተሽከርካሪ በፈንጂ ተመቶ ከኤርትራ ወደ አዲስ አበባ ለሕክምና መጥተው በጦር ኃይሎች ሆስፒታል ተኝተው ነበር። ጀ/ደምሴ በወቅቱ አዲስ አበባ በሚገኘው የመከላኪያ ሚኒስቴር የጦር ሐይሎች የዘመቻ ዋና መምሪያ ሐላፊ ነበር።

ወደ ኤርትራ የጦር አዛዥ ሆኖ ከመሄዱ በፊት መሆኑ ኑው። ወደ ጦር ሐይሎች ሆስፒታል ጀ/ደምሴ ጀ/ቁምላቸውን ሊጠይቅ ሄዶ ስለመንግሥት መወያየት ጀመሩ።

"ይህ መንግሥት መለወጥ አለበት። በዚህ ሁኔታ መቀጠል አንችልም። ሕዝብ እያሰጨረሰን ነው። አገሪቱን የአንድ ሰው አምባገነንነት እያደቀቃት

ነው። እኛ ተጠያቂ ነን። አንድ ነገር ማድርግ አለብን። ያንተ አቋም ምንድን ነው? ይህን ሚስጥር የማካፍልህ አቋምህ ከኔ አቋም ጋር ብዙም የተለየ አንዳልሆን በመገመትና በሚስጥር ጠባቂነትህም የምተማመን በመሆኑ ነው።" አለ ጀ/ደምሴ ወደ ጀ/ቁምላቸው የተጉበት አልጋ ጠጋ ብሎ በዝቅተኛ ድምጽ።

"የኔም አመለካከት ከዚህ የተለየ አይደለም። ይህ መንግሥት መውረድ አለበት። በዚህ አካሄዳችን የባሰ ማጥ ውስጥ እንጂ ለህዝቡ ሠላምና ብልጽግና እናመጣለን ብዬ አላምንም። ይህን መንግሥት ለመገልበጥ በሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ ተካፋይ ለመሆን ዝግጁ ነኝ።"

ጀ/ደምሴ "በጣም ጥሩ ነው በሚስጥር እንድትይዝው ላንተ መንገር እያስፈልገኝም ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ከኔ በሰተቀር ከማንም ሰው ጋር አትወያይ። መርዕድም ታሞ እዚሁ ለህክምና ገብቷል። ስሱ አቋምህን አሳውቀዋለሁ።" አለ ጀ/ደምሴ። ጀ/ቁምላቸው በጀ/ደምሴና በጀ/መርዕድ ንጉሤ መካከል የነበረውን ጥብቅ ወዳጅነት በሚገባ ሰለሚያውቁ ጀ/ደምሴ ያሉበት ንቅናቄ ውስጥ ጀ/መርዕድም መሳተፋቸው እንዳማይቀር ገምተው ነበር።

ከወራት በኋላ አፍአቤት የነበረው የናደው ዕዝ ሲደረመስና የኤርትራ ጦር በአዲስ መልክ ሲዋቀር ጀ/ደምሴ የጦሩ አዛዥ ጀ/ቁምላቸው ደግሞ አንዱ የጦሩ ምክትል አዛዥ በመሆን ተሹመው ወደ አስመራ ሲመደቡ በዚያች ቀን በጦር ሐይሎች ሆስፒታል ለተወያዩበት ዓላማ መሳካት አንደኛውን መንገድ ከፈተላቸው።

-15-

ግንቦት 8 ጠዋት ወደ ረፋዱ ላይ ጀ/ቁምላቸው ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ ተመልሰው ስለተደረገው ዝግጅት ማብራሪያ ለማቅረብ በቀጥታ ወደ ጀ/ደምሴ ቢሮ አመሩ።

ከቢሮ እንደደረሱ የተሰመደውን የወታደራዊ ሰላምታ ተሰዋውጠው የሄዱበት ዓላማ ግብ መምታቱን ማብራራት ጀመሩ።

"ከጀ/አበራ ጋር ትናንት አቤቱ ተገናኝተን ተወያይተናል። ዝግጁ ነው። ጠላይ የሚገኘውን የስፖርታ ክፍለ ጦር በጀ/ውበቱ በኩል ወደ አዲስ አበባ እንደሚያስመጣና እንደሚያስረክበኝ ተነጋግረን ጨርሰናል። በአየር ሐይል ያለውን ጀ/ፈንታ ጨርሰዋል። ጀ/ሰለሞን አውሮፕላኑን አስገድዶ አስመራ እንደሚያሳርፍ ካልሆነም መትቶ ለመጣል ያለውን ዝግጅት ጨርሷል። ከሁለቱ አንዱ የሚሆን ካልሆነ ኩዴታው አይደረግም በሚለው ተስማምተናል።" አሉ ጀ/ቁምላቸው፣ ስለ ኤርትራው ጦርነት ለሊቀመንበሩ ወይም መከላከያ ሚኒስትር ሪፖርት ለማቅረብ በሚል ሰም ከአስመራ አዲስ አበባ ሄደው ሲያቀናብሩ የቆዩትን አየተነተኑ።

ምሳ ሰአት አካባቢ ጀ/ደምሴና ጀ/ቁምላቸው በጀ/ደምሴ ቢሮ ሆነው የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ መጀመር ወይ መሠረዙን ለመስማት ከአዲስ አበባ የስልክ ጥሪ ይጠብቃሉ። መፈንቅለ መንግሥቱ

የሚሠረዝባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ነበሩ። መንግሥቱ ሐ/ማርያም የምስራቅ ጀርመን ጉዞውን በመጨረሻ ደቂቃዊች ሊሠርዝ ይችላል። የሚጓዝበት አውሮኘላን በታቀደው መሠረት በተለያየ ምክንያቶች ተገደ እንዲያርፍ ሳይደረግ ወይም ሳይመታ ከቀረም መፈንቅለ መንግሥቱ ሳይሞክር ለሌላ ቀን እንደሚተላለፍ በመወሰኑም እርግጥ በዚያ ቀን ሙከራው እንደሚደረግ መቶ በመቶ እርግጠኛ አልነበሩም። ከአዲስ አበባ የሚመጣውን ጥሪ ይጠባበቃሉ።

ሰልክ ተደወለ። ጀ/መርዕድ ነበር ከአዲስ አበባ መከላከያ ሚኒስቴር የደወለው። የጠሩ ጠቅላይ ኤታማጀር ሹም (ቺፍ ኦፍ ስታፍ) ስለሆነ ከመከላከያ ሚኒስትሩ ቀጥሎ ያለው ከፍተኛ መኮንን እሱ ነው።

"ደምሴ እንኳን ደስ ያለህ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ ነጻ ወጥቷል። አውሮኘላኑ ተመቶ ወድቋል። ሔሊኮኘተር ተከትሎ መውደቁን አጣርቶ ሪፖርት አድርጉልናል። ስለዚህ ቁምላቸውን ወደዚህ ላክው።" የሚል ነበር።

ጀ/ቁምላቸው ከጀ/ደምሴ ጋር ተቃቅፈው እንኳን ደስ ያለህ ከተባባሉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ለመዘጋጀት ወደ ቢሮአቸው አመሩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከጀ/ደምሴ ጥሪ ተደርጉላቸው እንደገና ለመነጋገር ወደ ጀ/ደምሴ ቢሮ ተመለሱ።

"ትንሽ ደስ ያላለኝ ነገር አለ። ለማንኛውም አንድ ሻምበል ጦር ይዘህ ብትሄድ ጥሩ ነው።" አለ ጀ/ደምሴ ፊቱ ላይ ትንሽ ቅሬታ አየታየ።

"የጠላዩ ጦር ገና እንቅስቃሴ አልጀመረም። ሌጣቸውን ነው የተቀመጡት ከአየር ወለድ ክፍለ ጦር አንድ ሻምበል ጦር በፍጥነት እንዲዘጋጀ አዝዣለሁ። አውሮኘላን ውስጥ ከገቡ በኋላ ግዳጃቸውን አሳውቃቸው። የኔንና የሁሴንን አጃቢዎች ከእንተ ጋር አልካቸዋለሁ። አዲስ አበባ እንደደረሳችሁ አኔ ቤት እንዲወርዱና እዚያው እንዲጠብቁ አዝዣለሁ።" አለ ጀ/ደምሴ።

"ከጀ/አበራ ጋር ተነጋግረን ጨርሰን? እንዴት ነው ይህ ነገር?" ብለው ጀ/ቁምላቸው ሲጠይቁ፤

"እንደደረስክ አበራን ኮንታክት አድርግና የሚመጣውን ጦር በእንተ ዕዝ ሥር አድርግና ተቀጣጠር። በል ጊዜ የለንም መልካም እድል።" ብሎ ጀ/ደምሴ ጀ/ቁምላቸውን ተሰናበተ።

ሌ/ኮ መንግሥቱ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ሲያብራሩ አዲስ አበባ ያሉት ጀኔራሎች አስመራ ላሉት መንግሥቱን ገድለናል ብለው ሳይነግሩ እንዳልቀሩ ጠቅሰዋል። (ሌ/ኮ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ትዝታ ገጽ 290)

ooo

አስመራ ከተማ ከሚገኘው የሬዲዮ ጣቢያ ግቢ አንድ ቶዮታ ላንድ ክሩዘርና መትረየስ የተጠመደበት ግልፅ ቶዮታ ፒክ አፕ ገብተው ቆሙ።

ጀነራል ደምሴ ከመኪናው ወርዶ ወደ ሬዲዮ ጣቢያው ገባ። የሬድዮ ጣቢያው ሠራተኞች ያልጠበቋቸው እንግዳ ነበሩ። ግንቦት ስምንት

1981 ወደ ከሰዓት በኋላ ነበር። የጣቢያው ኃላፊ የጀነራሉን መምጣት ሰምቶ ወደሳቸው አመራ።

"ዛሬ የምታስተላልፉት የተለየ መልዕክት አለ። የወትሮ ፕሮግራማችሁን አታስተላልፉም። ከዚህ በኋላ ከሁለሠ (ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት) በሚሠጣችሁ መመሪያ መሠረት ነው ሥራችሁን የምትቀጥሉት ከዚህ ሌላ የምታደርጉት ለውጥ የለም።" ሲናገር እርጋታ በተሞላበት ሁኔታ ነበር። የጣቢያው ሃላፊ በሰማው ተደናግጦ በሁኔታው ተገርሞ ትእዛዙን እንደሚፈጽም አስታወቀ።

ጀ/ደምሴ ጥቂት ወታደሮች በጣቢያው እንዲመደቡ አድርገው ወደ መኪናው በመጡበት አኳኋን በባሻ ክፈተው ሾፌርነት ወደ ቃኘው ሰተሽን ተመለሱ።

ooo

ኮ/መንገሻ ማክሰኞ ግንቦት 8 ቀን፣ ከጀ/ደምሴ ቢሮ ሰልክ እንደሚፈልጋቸው ሲነገራቸው ከወትሮው የተለየ ውይይት አልጠበቁም። በሁለተኛው አየር ምድብ የዘመቻ ሃላፊ ሆነው ለብዙ ጊዜ ሠርተዋል። በኤርትራ የነበረው የአየር ኃይል እንቅስቃሴ በሙሉ በእሳቸው ቁጥጥር ነበር የሚንቀሳቀሰው። ግንቦት 8 የበላይ አለቃቸው ብ/ጀ ንጉሤ ዘርጋው አዲስ አበባ ለስራ ሄደው ስለነበር፣ ኤርትራ ለሚገኘው ሁለተኛው አየር ምድብ የበላይ ኃላፊ እሳቸው ነበሩ። ሰልኩን ተቀብለው ከጀ/ደምሴ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ለእስቸኳይ ጉዳይ ስለሚፈለጉ ቢሮ ድረስ እንዲመጡ ጀ/ደምሴ ጠየቃቸው። ኮ/መንገሻም ትዕዛዙን ተቀብለው ከቀድሞ የተለየ ነገር አለ ብለው ሳያስቡ ወደ ጀ/ደምሴ ቢሮ አመሩ።

ጀ/ደምሴ ኮ/መንገሻን ሲያገኝ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው "ጉርባ" ብሎ በኦሮምኛ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ወደ ቁምነገሩ በቀጥታ ገባ።
"ዛሬ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ወደ ምስራቅ ጀርመን ለጉብኝት ሲሄድ የሚጀመር የመንግሥት ለውጥ ይደረጋል። ሁሉ ነገር በዝግጅት የተጠናቀቀ መሆኑ ተገልጸልኛል። ዝርዝሩ በኋላ የሚገለጽ ነው። አሁን አንተን እዚህ የጠራሁህ የማላውቅህ ነገር ስላለ ነው። የመንግሥቱ አውሮፕላን በአየር ላይ እንዳለ ከኢትዮጵያ ጠረፍ ሳይወጣ ኢንተርሴፕት ተደርጉ ተገደ እዚህ

እንዲመጣ ይደረጋል። ይህን የሚያደርጉ ሁለት ጀቶች ከደብረዘይት ይነሳሉ።

"ይህን አላደርግም ካሉ ደግሞ አውሮኘላኑ እንዲመታ ነው የተወሰነው። ስለዚህ ይህን ግዳጅ ያጠናቀቁት ፓይለቶች እዚህ መጥተው ነው የሚያርፉት። ከነሱ ምልክት እንዳገኘህ ታሳውቀኛለህ። እነሱን የሚጠብቁ የተወሰኑ ወታደሮች እንልካለን። የሚደርስህን መልእክት አሳውቀን። ይኸው ነው።"

ኮ/መንገሻ ጉዳዩ የተገለጸላቸው በትዕዛዝ መልክ ቢሆንም ዜናውን በደስታ ነበር የተቀበሉት። አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው ሰላምታ ሰጥተው ከጀ/ደምሴ ቢሮ ሲወጡ ገና የምሳ ሰዓት አልደረሰም።

ኮ/መንገሻ ከየቦታው የሚጉርፈውን የተለያየ መልእክት አጥብቀው ሲከታተሉ ቀኑ ወደ ምሽት ተለወጠ። ከተባሉት ጀቶች ምንም የመጣ መልእክት አልነበረም።

○○○

ግንቦት ስምንት የቢሮ ሠራተኛ ከየቢሮው በስጋት ወደቤ ሲራወጥ አዲስ አበባ የሚገኘው የመከላከያ ሚኒስቴር ዋና ፅህፈት ቤትፃ ከሌላው መሥሪያ ቤት ያልተለየ ግራ መጋባት ይታይበት ነበር። ከሌላ መ/ቤት የሚለይበት ማንኛውም ሠራተኛ አንዳይወጣ የወጣም አንዳይገ በመደረጉ ነበር።

የመከላከያ ሚኒስቴር የበላይ ሹማምንት ሌ/ኮ/መንግሥቱ ኃይለማሪያምን ወደ ምስራቅ ጀርመን ሽኝተው ከተመለሱ በኋላ ረጋ ባለ መንፈስ ወደ ሰራቸው ሲመለሱ ለቀኑ የታቀደውን የሚያውቁ ቢበዛ ከአምስት የበላይ ኃላፊዎች አይበልጡም ነበር። በተቀዳሚነት ጀ/መርዕድ ንጉሤ የመፈንቅለ መንግሥቱን በመሪነት ያቀነባበሩ፣ ሜ/ጀ/አበራ አበበ የመፈንቅለ መንግሥቱ የዘመቻ ኃላፊ ሆነው እንዲሰሩ የተመደቡ እንዲሁም የእነዚህ ጀነራሎች ረዳት መኰንኖች ብቻ ሚስጢሩን የተካፈሉበት ሁኔታ ነበር።

ሜ/ጀ/ አማሃ ደስታ መቼ የመፈንቅለ መንግሥት ሴራ ውስጥ እንደገቡ ብዙም ግልፅ አይደለም። የተወሰኑ ሰዎች እስክ አለቱ ድረስ አልተነገራቸውም ይላሉ። የአየር ኃይል ምክትል አዛዥ የነበሩት ብ/ጀ/ሰለሞን ግን ሰለ ጉዳዩ ቀደም ብለው ከሚያውቁት ውስጥ ነበሩ። ጀ/ሰለሞን ከሜ/ጀ ፋንታ በላይ ጋር በጣም የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው እና የቅርብ ወዳጅም ስለነበሩ ከጀ/አማሃ በፊት በአየር ኃይል በኩል የሚደረገውን በሙሉ እንዲያሟሉ ሐላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር።

ሜ/ጀ/አበራ አበበ በምስራቅ አዝ በኋላ አንደኛ አብዮታዊ ሠራዊት ተብሎ የሚታወቀው የምክትል አዛዥ ሆነው ሲሾሙ ጀ/ደምሴ የጦሩ ዋና አዛዥ ነበር። ከድሮ ጀምሮ የሚተዋወቁና የሚግባቡ ስለነበር አባቴ በጀ/አበራ ወደ ሐረር ተሹሞ መሄድ በጣም ተደስቶ ሲናገር ትዝ ይለኛል።

"አበራ በጣም ጉበዝ መኮንን ነው፣ የሱ ሐረር መምጣት በጣም ነው የሚረዳኝ" ይል ነበር። አብረው አሰራኤል አገር ለአየር ወለድ ትምሕርት ሄደው ከተመለሱ በኋላ አየር ወለድን ደብረ ዘይት አብረው ነው ያቋቋሙት። ጀ/አበራ ከአባቴ ጋር የመንግሥት ለውጥ መደረግ አማራጭ የሌለው እርምጃ መሆኑን መወያየት የጀመሩት ሐረር እያሉ በ7ዐዎቹ ዓመተ ምሕረት አጋማሽ አካባቢ ነበር። የጀነራል መኮንኖችን ምርመራ ካካሄዱት አንዱ ከአሰር ቤት ፅፎ አንዳሳተመው ከሆነ ጀ/አበራ የፃፉት ረቂቅ ፅሁፍ አንደሚገልፀው የመፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ አቅድ የጀመሩት ሐረር ከጀኔራል ደምሴ ቡልቶ ጋር በሚሠሩበት ጊዜ ነበር። *(ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ቁጥር 4)*

አባቴ ከ1ኛው ሠራዊት ጦር አዛዥነት ወደ አዲስ አበባ ተዛውሮ ሲመጣ የአዛዥነቱን ቦታ ለጀ/አበራ አሰረክቦ ነበር የለቀቀው።

ግንቦት ስምንት ከለዓት በኋላ የመከላከያ ሚ/ር ሠራተኞች በመሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲሰበሰቡ ከተደረገ በኋላ ጀ/መርዕድ ቀርበው የመፈንቅለ መንግሥት እንደተካሄደ ለተሰብሳቢው ገለፁ። የመከላከያ ሚ/ር የነበሩት ሜ/ጀ ሐይለ ጊዮርጊስ ሐብተማርያም ሰብሰባው ሲጠራ ያማከራቸው ሰው አልነበረም።

ከጀ/መርዕድ ቀጥሎ ጀ/አበራ ኮ/መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከሥልጣን እንደወረደና አዲስ መንግሥት እንደሚመሠረት የሚገልጽ መግለጫ አነበቡ።

ሰለ ሰብሰባው ሲሰሙ ከመከላከያ ወጥተው ወደ ቤተመንግሥት በመሄድ ሕገወጥ ሰብሰባ እየተካሄደ መሆኑን የገለፁት ጀ/ ኃ/ጊዮርጊስ እንደነበሩ ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ምርመራ ያካሄደው ሻምበል ፅፎታል። *(ተራሮችን ያንቀጠቀጠ በሚለው መጽሐፍ 4ኛ ክፍል።)* ሌሎች ደግሞ በአገር ውስጥ ደህንነት ኃላፊ በኮ/ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ጠቋሚነት ወደ መከላከያ ሚኒስቴር ሰብሰባውን ለማስቆም እንደተላኩ ይገልጻሉ። ያም ሆነ ይህ ሚ/ጀ/ሐይለጊዮርጊስ መከላከያ ሚ/ር ገብተው ሰብሰባው ህገ ወጥ እንደሆነና የተሰበሰበው እንዲበተን ለማዘዝ ሲሞክሩ ከጀ/አበራ ጋር ተጋጩ። በግጭቱ መሃል ሚኒስትሩ በጀ/አበራ ጥይት ተመተው ወደቁ። ጀነራል አበራም እስካሁን ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ከመከላከያ ሚኒስትር ግቢ ወጥተው ተሰወሩ።

በመከላከያ ሚ/ር የተደረገው ሰብሰባ ያለረዳት ጦር ጥበቃ ነበር። ይደርሳል ተብሎ የተጠበቀው ከጠላይ የሚመጣው ጦር አልደረሰም። ሌ/ኮ/መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ይዞ የተገኘዘው የአየር መንገድ አውሮኘላን ከኢትዮጵያ የአየር ጠረፍ አልፎአል። አውሮኘላኑ ከተነሳ በኋላ ተገደ ወደ አስመራ እንዲበርና አዚያው በግዳጅ ካረፈ በኋላ ሌ/ኮ መንግሥቱ በአስር አንዲውል አለበለዚያም በአየር ላይ አንዳለ በጦር አውሮኘላን አንዲመታ ነበር የታቀደው። ስለዚህ አቅድ ጀ/ቱምላቸውና ጀ/አበራ በሰፊው የተወያዩበት

ቢሆንም ውሳኔውን ተፈፃሚ የሚያደርጉት የአየር ኃይል ምክትል አዛዥ ጀነራል ሰለሞን ነበሩ። በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ ግን የአየር ኃይል አባላት- "ውሳኔው የብዙ ሰላማዊ ሰው ሕይወት አለ አግባብ አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነና የኢትዮጵያ አየር ኃይልንም ታሪክ የሚያበላሽ ስለሆነ እኛ ሁሉ ከተስማማን ሁኔታውን እዳር ለማድረስ የሚገታን ስለሌለ አውሮኘላኑን መምታት አያስፈልግም።" በማለት ውጥኑን ቀየሩት። ይህ ለውጥ የተደረገው በመጨረሻዋ ሰዓት ላይ በመሆኑ ሊሆን ይችላል አስመራ ለነበሩት ለጀ/ደምሴ እና ጀ/ቱምላቸው መንግሥቱ ኃ/ማርያም ተገድሏል ተብሎ የተነገራቸው። ቀደም ብለው የተሰማሙበትን በመጨረሻ ሰዓት ላይ ቀይረነዋል ከማለት ይልቅ ፣ጉዳዩ ያለቀለት ስለሆነ አንዲሁ የመንግሥቱ አውሮኘላን ተመቶ ወድቋል ብለን እንቀጥል። "በኋላ እናስረዳቸዋለን" የማለት ዓይነት ይመስላል።

በጀ/መርዕድና በጀ/ደምሴ መካከል የነበረው ቅርበት የወንድም ዓይነት ስለነበር መፈንቅለ መንግሥት ከተደረገ በኋላ "አይ እኛ እኮ ባለቀ ሰዓት ሌላ ጭቅጭቅ አንዳታመጣ ብለን ነው።" ብሎ ቀልዶ የሚያልፈው ዓይነት አድርጉ ሊወስደውም ይችላል። የኘላን ለውጥ ምን ያህል ጀ/ደምሴን አንደሚያበሳጭው ያውቃል። በየትኛውም ምክንያት ቢሆን የተላለፈው መልዕክትና አውነቱ የተለያዩ ነበሩ። የአስመራ ሬዲዮ ግንቦት 8 ወደ ማምሻው አካባቢ ያሰማውም ይህንኑ ከአውነት የራቀ ዜና ነበር። ምሽቱ አየተጋመሰ ሲሄድ ግን መንግሥቱ ተገድሏል የሚለው ሳይደገም "የ15 አመት ባርነት አክትሞአል" በሚለው ተተካ።

ooo

ጀ/ቁምላቸው አስመራ አውሮኘላን ማረፊያ ሞተራቸውን እያሞቁ፣ ከኋላቸው ያለውን ወደ ታች ወርዶ የሚከፈተውን ሰፊ በር አውርደው ወደሚጠብቁት የራሺያ አንቶኖቭ አስራ ሁለት አውሮኘላኖች ድረስ በተሸከርካሪ መኪናቸው ከቀረቡ በኋለ የሚጓዘው ጦር አውሮኘላን ላይ እንዲወጣ አዘው እሳቸውም ቦታቸውን ያዙ። ጠሩ ግራ ተጋብቶ ነበር። ለምን እንደሚሄድ፣ ወዴት እንደሚሄድ አልተነገረውም። ግዳጅ እንዳለው ተገልጾለታል። የቀረው አስካሁን ሚስጥር ነው።

አውሮኘላኖቹ በተከታታይ ተነስተው ጉዟአቸውን ጀምረዋል። በአየር ላይ ጥቂት እንደተጓዙ ጀ/ቁምላቸው ተነሱና ከያዙት የእጅ ቦርሳ ወረቀት አውጥተው ለተጓዡ እንዲከፋፈል አደረጉ። ጭንቅላቶች አዘቅዝቀው ያነቡና ቀና ብለው በመገረም ይተያዩ ጀመር።

ወዲያው አንዱ ወታደር ማጨብጨብ ጀመረ። ሌሎችም ተከተሉት፤ አውሮኘላኑ ውስጥ የነበረው ወታደር በሙሉ ባንዲ ጭብጨባውን አቀለጠው። ወረቀቱ በአጭሩ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም አምባገነን አገዛዝ ማብቃቱንና መንግሥቱ ተገድሎ ከሥልጣን መውረዱን እንዲሁም ጠሩ አዲስ አበባ ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን ለመቆጣጠርና ሰላም ለማስከበር እንደሚጓዝ የሚገልጽ ነበር።

ከጀ/ቁምላቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ ከተጓዙት ውስጥ ሁለት የጀ/ደምሴ አጃቢዎች ከሁለት የጀ/ሁሴን አጃቢዎች ጋር በመሆን ቦሌ አውሮኘላን ማረፊያ እንደደረሱ በተዘጋጀላቸው የጭነት መኪና ከሌሎች ወታደሮች ጋር በመሆን ቦሌ ድልድይ ጋር ሲደርሱ ወደ ግራ በመገንጠል የጀ/ደምሴ መኖሪያ ቤት ወርደው ወደ ውስጥ ገቡ። የጭነት መኪናው የቀሩትን ወታደሮች ይዞ ወደ ዋናው መንገድ በመመለስ ወደ አብዮት አደባባይ አቅጣጫ አመራ። የተወሰነው የጭነት መኪና ወደ አብዮት አደባባይ ሲጓዝ የተወሰነው ደግሞ በውሎ ሰፈር አድርጉ ወደ አርሚ አቪየሽን የጦር ሠራዊት አውሮፕላን ማረፊያ አመራ።

ጀ/ቁምላቸው ወደ አርሚ አቪየሽን ካመራው ክፍል ጋር ነበሩ። እዚያ እንደደረሱ የአዛዡ ቢሮ ገብተው የተለያዩ ጦር ክፍሎችንና መሪዎችን በሬድዮና በስልክ ማነጋገር ጀመሩ። ጀ/ቁምላቸው አዲስ አበባ ከደረሱበት ደቂቃ ጀምሮ ጥረት አያደረጉ የነበረው ጀ/አበራን ለማግኘት ነበር። መልስ አላገኙም። አዲስ አበባ ሲደርሱ የመፈንቅለ መንግሥቱ ተባባሪ ናቸው በተባሉት በኮ/ተስፋዬ ወልደ ሥላሴ አቀነባባሪነት መከላከያ ሚኒስትር በልዩ ጥበቃ ብርጌድ ተከቦ ነበር የጠበቃቸው። ኮ/ል ተስፋዬ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ደጋፊነት ወደ ተቃዋሚነት እንዴት እንደተቀየሩ ለጀ/ቁምላቸው ግልጽ አልነበረም። መከላከያ ሚኒስቴር በተደጋጋሚ ደውለው ያገኙት መልስ "ተከበናል ከቻላችሁ አጥቁና እርዳታ አድርጉልን" የሚል ነው።

"የሚመጣው ጦር የታለ?" አጥጋቢ መልስ አላገኙም። ከዚያም ቀጥለው ይመጣል ተብሎ ከነበረው ጦር አዛዥ ብ/ጀ ውበቱ ጋር በሬዲዮ ይገናኛሉ።

ጀ/ውበቱ የደረሳቸው ትዕዛዝ አለመኖሩን ይገልጹና ጦር ይዞ አዲስ አበባ ለመምጣት ከአለቃቸው ትዕዛዝ ካልደረሳቸው በስተቀር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ይገልጻሉ። ይህ ለጀ/ቄምላቸው አንግዳ ነበር። በጀ/አበራ ትዕዛዙ እንደተላለፈ ነው የሚያውቁት። አሁን ጀ/አበራ ሊገኙ አልቻሉም። ቢቸግራቸው ከሐረር ተጨማሪ ጦር ይመጣል ተብሎም ስለነበር የምስራቅ ዕዝ ምክትል አዛዥ ወደነበሩት ብ/ጀ/ጌታቸው ገዳሙ ይደውሉና ወደ አዲስ አበባ ጦር እንዲልኩ ይጠይቃሉ። ጀ/ጌታቸው ገዳሙ እና ጀ/ቄምላቸው አንድ ኮርስ የነበሩና ለብዙ አመት የሚተዋወቁ በመሆናቸው ጀ/ቄምላቸው እንደ ቅርብ ጓደኛ ነበር የሚቆጥሯቸው ጀ/ጌታቸው ገዳሙ ሊተባበሩ ፈቃደኛ አልነበሩም። ከሐረር ጦር ለማምጣት ዝግጅት እንደነበረና ላኪው በመጨረሻ ደቂቃ ሐሳቡን ቀይሮ የተባለው ጦር እንዳልመጣ በሌሎች ሰዎች ተመዝግቧል።

በመጨረሻም ጀ/ቄምላቸው ቀድሞ ከጀ/መርዕድ ንጉሤ በተነገራቸው መሠረት የፖሊስ አዛዥ የነበሩት ጀ/ውርቁ ዘውዴን ፍለጋ ይጀምራሉ። የፖሊስ ኮማንዶ በመፈንቅለ መንግሥቱ ለመተባበር ዝግጁ ሆኖ የማቆየት ስራ የጀ/ውርቁ ዘውዴ ነበር። እርሳቸውም በቦታው የሉም። ሁኔታው ተበላሽቷል። ምሽቱ እየተጋመሰ ነው። ኩዴታው ከሸፈ የሚል ዜና መናፈስ ጀምሯል። ጀ/ቄምላቸው ይዘው የመጡትም ጦር ግራ እየተጋባ መጣ። የተነገራቸውና በቦታው ላይ ያገኙት አንድ አልሆነም። ጀ/ቄምላቸው በብዙ ውይይታችን ጊዜ ግልጽ ባላደረጉት ሁኔታ ከጦሩ ተለይተው ተሰወሩ። ጸሐይ ገብታ ሳትወጣ ይዘው የመጡት ጦር እጁን ሰጥቶ አዲስ አበባ የነበረው

አንቅስቃሴ በጀቶች ጩኸትና በሕዝብ ጭምጭምታ ወረ ተድበሰበሰ አለቀ።